# የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ማዕቀፍ (Frame work)

*ተሻሽሎ የተዘጋጀ*

**ግንቦት 2003 ዓ.ም**

**ትምህርት ሚኒስቴር**

# ማ ው ጫ


ገጽ

I. መግቢያ ........................................................................ 1

II. የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ምንነትና ዓላማ ......... 2

III. የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ማዕቀፍ (Framework).. 4

IV. የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ስታንዳርድ ……………. 9


## ተቀፅላዎች


ተቀፅላ 1፡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር የግለ ግምገማ ፎርም ........................................................... 22

ተቀፅላ 2፡ የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያዎች ………………….. 61

ተቀፅላ 3፡ የት/ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር የትግበራ ክትትልና የግምገማ አባሪ ቅፃቅፆች ………………….. 74

ተቀፅላ 4፡ ልዩ ልዩ የክትትል መዝገቦች ቅፃቅፆች ………………. 82

## I. መግቢያ

የትምህርት ጥራትን በተጨባጭ ዕውን ለማድረግ ትምህርት ቤቶች መሰረት እንደመሆናቸው አሰራራቸውን ማሻሻል አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑ ዕሙን ነው።

በመሆኑም የትምህርት ሚኒስቴርና የክልል ባለሙያዎች በጋራ በመሆን በትምህርት ቤት ደረጃ የትምህርት ተገቢነትና ጥራትን ለማረጋገጥ እንዲቻል በሀገራችን ካሉት ትምህርት ቤቶች መልካም ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና ከሌሎች ሀገሮች ከተገኘው ልምድ ጋር በማጣጣም በሁሉም ትምህርት ቤቶች በሰፊው ለመተግበር እንዲቻል ይህንን የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ማዕቀፍ (School Improvement programme framework) አሻሽለው አዘጋጅተዋል።

የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ማዕቀፍን በሀገራችን እንዲተገበር በማድረግ ሁሉም የትምህርቱ ሥራ ባለድርሻዎች በትምህርት ቤት ደረጃ ትምህርቱን በጥራት ለመስጠት እና የተማሪዎች የመማር ውጤት (Learning Outcomes) ላይ በጎ/አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የትምህርት ቤት አቢይ ርዕሰ ጉዳዮችን (Domains) በመለየት እንዲሁም፤ ለእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ግብ በማስቀመጥ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታና ውጤት የማሻሻል ተግባር ላይ አቅደው በጋራ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የሚፈለገው የጥራት ደረጃ ላይ ለመድረስ ያስችላል።

በዚህ ሰነድ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ምንነትና ዓላማ በውስጡ ያካተታቸው የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ዐብይና ንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ስታንዳርዶች፣ ግለ ግምገማ ለማካሄድ የሚያገለግሉ የግለ ግምገማ ቅጾች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች እና ልዩ ልዩ የክትትልና ሪፖርት ማጠናቀሪያ ቅጾች ቀርበዋል። ስለዚህ ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሙን ተፈፃሚ ለማድረግ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ይህን ሰነድ /ማዕቀፍ/ ከትምህርት ቤታቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንዲጠቀሙበት ያስፈልጋል።

## II. የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ምንነትና ዓላማ

የትምህርት ቤት መሻሻል (School Improvement /Programme) ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ የትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮች (Domains) አንፃር ግለ ግምገማ (self-evaluation) በማካሄድ የትምህርት ግብዓቱንና ሂደቱን በማሻሻል ተማሪዎች የላቀ የትምህርት ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ ላይ ያተኮረ ፅንሰ ሀሳብ ነው።

የትምህርት ቤት መሻሻል ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን ባህርይ እና የመማር ሁኔታ በማሻሻል የመማር ውጤታቸውን (Learning Outcome) በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ነው። ይህም ማለት ተማሪዎችን በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት፣ ብቁ እንዲሆኑ ማስቻል ማለት ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ትምህርት ቤቶች በቅድሚያ ጠንካራ ጐናቸውንና መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች /ደካማ ጐናቸውን/ መለየት ይገባቸዋል። ለተማሪዎቹ ትምህርት መቀሰምና ውጤታቸው ከፍተኛ መሆን በጎ /አምንታዊ/ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ የትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮችም አንፃር ግብ በማስቀመጥ እና ቅድሚያ ትኩረት (Priorities) በማውጣት ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላትና ሌሎች ባለድርሻዎች ለተማሪዎቹ መማርና የመማር ውጤቶች ከፍተኛ መሆን በጋራ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ይህ ሂደት የማያቋርጥና ዑደታዊም ነው።

በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች መማርና የመማር ውጤቶች በጎ ተፅዕኖ የሚያሳድሩት የትምህርት ቤት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች (Domains) በጥናት ላይ በመመርኮዝ ተለይተው የታወቁ ሲሆን፣ እነሱም በአራት ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. መማርና ማስተማር
2. የትምህርት ቤት አመራር
3. ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ
4. የኅብረተሰብ ተሳትፎ ናቸው።

እነዚህ አበይት ርክሰ ቶ□□ች በሥራቸው የተለያዩ ንዑሳን ጉዳዮች (Elements) አሏቸው:: ለእያንዳንዱ ንዑስ ቶ□ይም በአንፃሩ በስታንዳርድነት የሚያገለግሉ ዝርዝር መቶለ□ ባህሪያት (Characteristics) እንዲኖራቸው ተደርጓል::

እነዚህ የተማሪዎች መማርና የመማር ውጤቶች ላይ በጎ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቤት ዐበይት ርዕሰ ጉዳዮች ምንነትና ያላቸው ተያያዥነት የሚከተለውን ይመስላል።

### የትምህርት ቤት ዐበይት ርዕሰ ጉዳዮችና ንዑሳን ጉዳዮች

**መማርና ማስተማር**

- የማስተማር ተግባር
- መማርና ግምገማ
- ሥርዓተ ትምህርት

**ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ**

- የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ
- ተማሪን ማብቃት
- ለተማሪ የሚደረግ ትኩረት

**የተማሪዎች ውጤት**

**የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር**

- ስትራተጂክ ራዕይ
- የአመራር ባህርይ (Leadership behavior)
- የትምህርት ቤት ማኔጅመንት

**የህብረተሰብ ተሣትፎ**

- ከወላጆች ጋር አብሮ መሥራት
- ኅብረተሰቡን ማሣተፍ
- የትምህርትን ሥራ ማስተዋወቅ

ከላይ ለማየት እንደሚቻለው ተግባራቱ እርስ በርስ የሚገናኙ፣ የሚደጋገፉና ወደ አንድ አቅጣጫ ማለትም የትምህርት ቤት መሻሻልን አልመው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። የትምህርት ቤት መሻሻል መቶለ□ □· □ተማሪዎች ውጤት መሻሻል ነው:: ስለዚህ የትምህርት ቤት መሻሻል መሠረ□ዊ ግ□ም እነኚህን አራቱን ቁልፍ መሠረታዊ የትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮች በተጠናከረ መልኩ ማከናወንና የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል ነው።

እነዚህን ተያያዥነትና ተደጋጋፊነት ያላቸውን የትምህርት ቤት ጉዳዮች መሠረት በማድረግ በአገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ስታንዳርዶች ተዘጋጅተዋል። ስታንዳርዶቹ ሊደረስባቸው የሚችሉ ነገር ግን የሁሉንም ባለድርሻዎች በባለቤትነት መንፈስ በጋራ መንቀሳቀስን የሚጠይቁ ናቸው።

## III. የትምህርት ቤት መሻሻል ማዕቀፍ (Frame work)

የት/ቤት መሻሻል ማዕቀፍ ት/ቤቶች በወጡት ስታንዳርዶች መሰረት ምን ያህል ውጤታማ መሆናቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ መሣሪያዎችንና ሂደቶችን የያዘ ሥርዓት (System) ነው። ማዕቀፉ ት/ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ምን እንደሚመስል በተለያዩ ተጨባጭ መረጃዎች የሚያውቁበት፣ ወደፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለይተው ማወቅ የሚችሉበት እና ምን ዓይነት ተጨባጭ የሆነ ውጤት ለማምጣት እንደሚፈልጉ አቅደው የሚንቀሳቀሱበት የትግበራ መመሪያ የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በዋናነት የሚከተሉት መሣሪያዎች ይገኙበታል።

1. በአበይት የት/ቤት ርዕስ ጉዳዮች አንጻር ት/ቤቶች ራሳቸውን ገምግመው ያሉበትን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችሏቸው የግምገማ መሣሪያዎች፣
2. የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ሠራተኞች እንዲሁም ከወላጆች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መሣሪያዎች፣
3. በተለያዩ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለመሰብሰብ፣ለማጠናቀርና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ቅጾች ናቸው።

ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሱትን መሣሪያዎች በመጠቀም በአጠቃላይ ግለ ግምገማ ማካሄድ፣ ማቀድ፣ መተግበር፣ መከታተልና መቆጣጠር፣ መመርመርና መከለስ እንዲሁም ለባለድርሻዎች ሪፖርት ማድረግ ያስችላቸዋል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ ሂደት የማያቋርጥ፣ ዑደታዊና በየሦስት ዓመቱ ጉዳዩ በሚመለከተው ከትምህርት ቤት ውጭ ባለ አካል ግምገማ ተካሂዶበት በሚሰጠው አስተያየት መሠረት (ትምህርት ቤቱ በየዓመቱ በራሱ ግምገማ መሠረት ማስተካከያ ከሚያደርገው በተጨማሪ) ማስተካከያ እየተደረገበት የሚከናወን ነው።

ይህን ዑደታዊ ክንውን በሚከተለው አኳኋን መግለጽ ይቻላል።

## የትምህርት ቤት መሻሻል ዑደት



ይህን ዑደታዊ ክንውን የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረበውን ማብራሪያ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

## ሀ. በመጀመሪያው ዓመት የሚከናወኑ፡-

1. ዝግጅት፡-

- የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ (School Improvement Committee) የትምህርት ቤት መሻሻል ማዕቀፉ እንዴት ሊተገበርና ሊመራ እንደሚችል ይወስናል።
- በትምህርት ሥርዓቱ በየደረጃው ያሉ የትምህርት ቤት መሻሻል ክትትል ኮሚቴዎችና ኃላፊዎች ለማዕቀፉ ትግበራና ትምህርት ቤቶች ለሚያደርጉት ዝግጅት ድጋፍ ይሰጣሉ።

2. በትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮች (School Domains) አንፃር መረጃ መሰብሰብ፡-

ትምህርት ቤቶች የሥራ አፈጻጸማቸውን በቅድሚያ በአራቱ አበይት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ይገመግማሉ።

3. የሲስተም ዳሰሳ (System Survey) ማከናወን፡-

ሲስተም ዳሰሳ የወቅቱን የትምህርት ቤቱን የሥራ አፈፃፀም አስመልክቶ ሁሉም ቁልፍ ባለድርሻዎች ማለትም፤ ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች ስላላቸው አመለካከት (Views) የሚቃኝበት ሂደት ነው። በዳሰሳው ትምህርት ቤቶች በአራቱም ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር ግብረ-መልስ (feed back) የሚቀበሉበት ወይም የሚሰበስቡበት የማይታለፍ ዋና ተግባር ነው።

4. የተሰበሰበውን መረጃ በጥንቃቄ በማየትና በመመርመር ስለትምህርት ቤቱ ሥራ አፈጻጸም ደረጃ ውሣኔ/ስምምነት ላይ ይደረሳል።

በትምህርት ቤቱ የሚመለከታቸው ቁልፍ የሆኑ ባለድርሻዎች በየዓመቱ በሚካሄደው የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። የተሰበሰበውን መረጃ በጥንቃቄ በመመርመርና ውሳኔ በመስጠትም ተግባር ቁልፍ የሆኑ ክፍሎች ይሳተፋሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የትምህርት ቤት መሻሻል ማዕቀፍ ትግበራ ከመማር-ማስተማር ሥራ ጋር ይቆራኛል።

5. የትምህርት ቤት ዕቅድ ማዘጋጀት

የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ በግምገማ የተገኘውን ውጤት (መረጃ) መሠረት በማድረግ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የሚያገለግል ዕቅድ ያዘጋጃል። ዕቅዱ ግቦችንና ዝርዝር ዓላማዎችን እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን (priorities) ያካትታል። አንድ ትምህርት ቤት ከሶስት ዓመት በላይ የሚያገለግል ዕቅድ ሊያዘጋጅ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው አዳዲስ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ዕቅዱን ሊያሻሽል ይችላል።

6. የትምህርት ቤትን ዕቅድ መተግበር

የዕቅድ ትግበራ የሚጀምረው የትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ ዕቅዱ ለትግበራ ዝግጁ ነው ብሎ ሲያምን ነው። ይህም ማለት ከቀድሞው ዕቅድ ወደ ተሻሻለው አዲሱ ዕቅድ የተሳካ ሽግግር ሲኖር ነው።

7. ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ

ኮሚቴው ራሱና በሥሩ በሚያቋቁማቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች አማካኝነት የክትትልና ቁጥጥር ተግባሩን ያከናውናል

8. የአፈጻጸም (የክንውን) ሪፖርት ማድረግ

የትምህርት ቤቱ ኮሚቴ ዓመታዊ ሪፖርቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል።

## ለ. በሁለተኛው ዓመት የሚከናወኑ

1. ትምህርት ቤቶች ያሳዩትን መሻሻል ቀደም ሲል ከተቀመጡት ግቦችና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንፃር ግምገማ ያካሂዳሉ።
2. በመጀመሪያ ዓመት ያልተከናወኑ ትግበራ ጠቋሚዎች ካሉ ይመረጣሉ።
3. ቅድሚያ የሚሰጣቸው አዲስ ጉዳዮች ካሉ ይለያሉ። በዚህ መሠረት የማቀድ፣ የመተግበር፣ የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ይከናወናሉ።
4. የትምህርት ቤቱ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል።

## ሐ. የሶስተኛው ዓመት ክንውኖች

1 ትምህርት ቤቶች ያሳዩትን መሻሻል በግለ-ግምገማ ይቆጣጠራሉ።
2. የትምህርት ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ትግበራ ይቀጥላል።
3. ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።
4. የትምህርት ቤቶች አሠራርና ውጤት ከትምህርት ቤቱ ውጭ በሆነ አካል ተገምግሞ ተጨባጭ የሆነ ምላሽ (feedback) ይሰጣቸዋል።ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን በመለየት የማሻሻያ አስተያየት (Recommendation) በትምህርት ቤቶቹ የተሰበሰበው መረጃ ተጨባጭነት ይረጋገጣል። የውጪ አካል ሪፖርት ለትምህርት ቤቱ ይቀርባል።

ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ተግባራት ለማከናወን የሚያስችሉ የተለያዩ መሣሪያዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በትምህርት ቤት መሻሻል ማዕቀፍ ትምህርት ቤቶች፣

- የተማሪዎቻቸውን ውጤቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲችሉ
- አበይት የትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮችን ለመለካት እና
- የማሻሻያ ዕቅድ ለመንደፍ የሚያደርጉትን ጥረት ለማሳካት ይረዳቸዋል።

በተጨማሪም ማዕቀፉ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ዕኩል የሆነ የመማር ዕድል ለመስጠት የሚያስችል ድጋፍና መመሪያ ይሰጣል። በአጠቃላይ የትምህርት ቤት መሻሻል ማዕቀፍ ሂደትና ውጤት ትምህርት ቤቶች የማያቋርጥ፣ ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ የመሻሻል እንቅስቃሴዎች እንዲያደርጉ እና ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ፣ ለወላጆችና ለመንግስት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሥርዓት ሊያሰፍን የሚችል አሠራርን ያቀፈ ነው።

## IV. የትምህርት ቤት መሻሻል ስታንዳርድ

በአገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ስታንዳርዶች ከነትግበራ ጠቋሚዎቻቸው በአራት ዐቢይ ርዕሰ ጉዳዮችና በአሥራ ሁለት ንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ተከፍለው ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

### ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 1፦ መማርና ማስተማር

ጥራት ያለው መማርና ማስተማር በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ የወደፊቱን ያገናዘበና ችሎታው የዳበረ የተማረ ማህበረሰብ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ መምህራንና ተማሪዎች የላቀ ብቃት (excellence) ለመሻትና ዕምቅ ችሎታቸውን ለመጠቀም ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ክንውን ነው።

**ንዑስ ጉዳይ 1.1፦ የማስተማር ተግባር**

**ስታንዳርድ 1 ፦ የመምህራን እውቀት፣ ክህሎትና እሴቶች በተለያዩ ስልጠናዎች አድገው በማስተማር ተግባር ጥቅም ላይ ውለዋል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.1.1 ትምህርት ቤቱ ጥራት ላለው መማርና ማስተማር ጠንካራ መሠረት የሚጥሉ በጋራ የተዘጋጁ እሴቶች አሉት።

1.1.2 መምህራን ተማሪዎቻቸው የተለያየ የመማር ፍጥነት እንዳላቸው በመቀበል የማስተማር ዘዴዎቻቸውን በዚሁ መሠረት አስተካክለው በመጠቀም የተማሪዎቹን ውጤት አሻሽለዋል።

1.1.3 መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ማብራሪያዎችና መግለጫዎች ቀላልና ግልጽ ናቸው።

1.1.4 መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ተምሳሌት ናቸው። ለተማሪዎቻቸው አስፈላጊውን ክበሬታ ስለሚሰጧቸው ተማሪዎቻቸው የደህንነትና በራስ የመተማመን ስሜት አድሮባቸዋል።

1.1.5 መምህራን ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመው ቀደም ብለው ለይተው ድጋፍ በመስጠታቸው የትምህርት አቀባበላቸው ተሻሽሏል።

1.1.6 መምህራን በልዩ ፍላጐት፣ በፆታ፣ በሃይማኖትና በዘር ላይ የተመሠረተ አንዳችም ልዩነት ሳያደርጉ የሁሉንም ተማሪዎች መብት በዕኩልነት ያከብራሉ፣ ተገቢውንም ድጋፍ ይሰጣሉ።

1.1.7 መምህራን ለተከታታይ የሙያ መሻሻል መሠረት የሚሆናቸውን እንደተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም (CPD)፣ የርስ በርስ ልምድ ልውውጦች፣ አጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠናዎችንና ሌሎች ለሙያ ማሻሻያ ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችንና መዋቅሮችን በመጠቀም የማስተማር ብቃታቸውን አሻሽለዋል።

1.1.8 መምህራን ሥራዎቻቸውን መልሶ ለመመርመርና ለማጥራት የተሰጧቸውን ተገቢ አስተያየቶች ተጠቅመው አፈጻጸማቸውን አሻሽለዋል፣

1.1.9 የትምህርት ቤቱ መምህራን በሚያወጡት ዓመታዊና ዕለታዊ ዕቅዳቸው መሠረት ማስተማራቸው ተረጋግጧል።

1.1.10 መምህራን ከተማሪዎቹ፣ ከመማር አውዱ (Learning context)፣ ከትምህርት ይዘት፣ ከተፈላጊው ዓላማና ውጤት አኳያ ተገቢነት ያላቸውን የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና ስትራተጂዎችን ተጠቅመው በማስተማራቸው ተማሪዎች ረክተዋል።

1.1.11 መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ጥሩ እውቀት አላቸው፤ ይህንንም እውቀታቸውን በክፍል ውስጥ በብቃት ተግባራዊ በማድረጋቸው የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል የተሻለ ሆኗል።

**ስታንዳርድ 2 ፦** መምህራን ያላቸውን ሙያዊ ዕውቀት በሚገባ በመጠቀም፣ በሙሉ ፍላጐትና በቁርጠኝነት በመሥራት እንዲሁም ከተማሪዎቻቸው ብዙ በመጠበቅ (High expectations) ለማስተማር ተግባሩ መሠረት በማድረግ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.1.12 የመምህራንን የማስተማር ተግባር ለማዳበር (ለማጐልበት) የሚረዱ ወቅታዊ ጥናትና ምርምርን መሠረት ያደረጉ መንገዶች (Procedures) አሉ።

1.1.13 መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤት ለማሻሻል አቅደው በመንቀሳቀሳቸው የተቀመጠውን ግብ አሳክተዋል ።

1.1.14 መምህራን እየተካሄደ ላለው የሙያ ማሻሻያ ትምህርት ያላቸው ቁርጠኝነት በንቁ ተሳትፏቸው ተረጋግጧል።

**ስታንዳርድ 3፡-** መምህራን ተማሪዎችን ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማገናኘት እንዲመራመሩ በማድረጋቸው የመማር ማስተማሩ ሥራ ተጨባጭ ሆኗል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.1.15 ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ በሚያስችላቸው ህብረተሰብን መሠረት ባደረጉ ፕሮግራሞችና በትምህርት ቤት ክለቦች ተሳተፉዋል።

1.1.16 መምህራን የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎቻቸው ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮቻቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አድርገዋል፣

**ንዑስ ጉዳይ 1.2፡- መማርና ግምገማ**

**ስታንዳርድ 4፡-** ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች የላቀ ውጤት መምጣት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ለውጤት መሻሻል መሠረት ሆኗል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.2.1 የደረጃ ማነፃፀሪያ ነጥቦች (Benchmarks) በግልጽ ተለይተው ተቀምጠዋል። ይህም በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በሙሉ እንዲታወቅ በመደረጉ ለግቦች መሳካት የበኩላቸውን ድርሻ አበርክቷል።

1.2.2 የተማሪዎች የውጤት መረጃ ቀደም ሲል ከነበረው የመነሻ ነጥብ (ውጤት) የተሻሻለ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል።

1.2.3 ከትምህርት ቤትና ከክፍል ግለ - ግምገማ የተሰበሰበው ዳታ ስለጠንካራ ጎኖችና ወደፊት ትኩረት ሊደረግባቸው ስለሚገቡ ደካማ ጎኖች መረጃ ለማመንጨት ተተንትኗል።

1.2.4 ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎች የሚጠብቀው ከፍተኛ ውጤትና የባህሪ ደረጃ እንዳሉት ከዳሰሳ ጥናት የተገኙ መረጃዎች አረጋግጠዋል።

**ስታንዳርድ 5፡-** ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ለትምህርት ተነሳሽነት ያላቸውና በንቃት የሚሳተፉ ሆነዋል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.2.5 መምህራን አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በመጠቀማቸው የተማሪዎች የክፍል ትምህርት ተሳትፎ አድጓል።

1.2.6 ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ደከም ያሉበትን ሁኔታዎች በመለየት የማሻሻያ ስልት ቀይሶ በመንቀሳቀሱ ውጤታቸው ተሻሽሏል።

**ስታንዳርድ 6፡-** የግምገማ ተግባራትና ሪፖርቶች ለተሻለ የትምህርት አሰጣጥና የመማር ውጤት መምጣት ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.2.7 መምህራን የተማሪዎቹን ዕድሜና ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች በመጠቀም የትምህርቱን አሰጣጥ አሻሽለዋል።

1.2.8 ከግምገማ የተገኙ መረጃዎችን ትምህርት ቤቱ የወደፊት እቅድና ፕሮግራም ለመንደፍ ተጠቅሞባቸዋል።

1.2.9 ለተማሪዎች ተገቢው ግብረ-መልስ (feed back) ለመሰጠቱ ማረጋገጫ መንገድ አለ።

1.2.10 ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት (መማር) ግምገማ ላይ ተሳትፈዋል፤ የራሳቸውንም ትምህርት (መማር) በመገምገም ለወደፊቱ ትምህርታቸው አቅደዋል (ግብ ጥለዋል)።

1.2.11 የግምገማ ውጤትና መረጃ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን መማርና ማስተማሩን ለማሻሻል ጥቅም ላይ ውሏል።

1.2.12 ለወላጆች የተደረገው ሪፖርት ስለ ልጆቻቸው የትምህርት ውጤት ስላሳዩት የባህሪይ ለውጥ እድገት ገንቢ አስተያየቶችን የሰጠ ነው።

**ንዑስ ጉዳይ 1.3፡- ሥርዓተ ትምህርት**

**ስታንዳርድ 7፡-** ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣ አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ ለመሆኑ የመመርመርና የማሻሻል ሂደቶች አሉ።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.3.1 የሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች (ሲለበስ፣ የተማሪ መፅሐፍና የመምህሩ መምሪያ ማጣቃሻ መፃህፍት፣ የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች) ከተማሪዎቹ ዕድገት ደረጃና ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ፣ ከማናቸውም አድልዎ ነፃ የሆኑ ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ተገቢነት ያላቸውና የሚያሳትፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በመምህራን ግምገማና ማሻሻያ ተደርጐባቸው ጥቅም ላይ ውለዋል።

## ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 2፦ ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ

ሁሉንም በዕኩልነት የሚያይ፣ መልካም አቀባበል የሚያደርግ ማህበረሰብ ያለው ትምህርት ቤት ርስ በርስ በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነቶችን ያጎለብታል። ለእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጐት ተስማሚ የሆነና ምቹ የሆነ አካባቢ ሊፈጠር ይገባል። ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የደህንነት ስሜት ከተሰማቸው ትምህርታቸውን በፍላጎት ይከታተላሉ። ተማሪዎች ስለትምህርታቸው ጉዳይ ውሳኔ በመስጠት ተሳትፈው የራሳቸውን አስተዋጽዖ ማበርከት እንዲችሉ አቅማቸው እንዲጎለብትና ድምፃቸውም ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ ይገባል።

**ንዑስ ጉዳይ 2.1፦** የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ (School Facilities)

**ስታንዳርድ 8፦** ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ የጠበቁ ፋሲሊቲዎችን በማሟላቱ የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ ለማከናወን፣ ተማሪዎችም ለመማር አስችሏቸዋል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

2.1.1 ትምህርት ቤቱ በአጥር የተከበረ ሳቢና ማራኪ የሆነ ግቢ ያለው በመሆኑ ተማሪዎችን አዘወትረው በትምህርት ገበታቸው እንዲገኙ አስችሏል፡፡

2.1.2 መማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁና ምቹ በመሆናቸው የተማሪዎቹን የመማር ፍላጐት አነሳስተዋል።

2.1.3 ትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማር ሥራ ደጋፊ የሆኑና ደረጃቸውን የጠበቁ በተገቢው ቁሳቁሶች የተሟሉ (የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ቤተ-ሙከራ

/ሳይንስ ኪት፣ ቤተ-መፃህፍት፣ የመምህራን ማረፊያ፣ የስፖርት ሜዳዎች ወዘተ…) ያሉት በመሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ ሆኗል።

2.1.4 በትምህርት ቤቱ ደረጃቸውን የጠበቁና በፆታ የተለዩ መፀዳጃ ቤቶች፣ የውሃ አገልግሎት ተዘጋጅተው ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ግልጋሎት በመስጠታቸው ተጠቃሚዎች ረክተዋል። የባህሪ ለውጥም አሳይተዋል፡፡

2.1.5 በት/ቤቱ ለመማር ማስተማሩ ሥራ አገልገሎት የሚውሉ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማቴሪያሎች /ሬዲዮ፣ ቴፕ፣ ፕላዝማ፣ ኮምፒዩተር ወዘተ./ ተሟልተው አገልገሎት ሰጥተዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 2.2፦** ተማሪን ማብቃት (Student Empowerment)

**ስታንዳርድ 9፦** ትምህርት ቤቱ የተለያዩ የአደረጃጀቶች የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋቱ በተማሪዎች ዘንድ ኃላፊነትን የመውሰድና ራስን በዲሲፕሊን የመምራት ልምድ ዳብሯል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

2.2.1 ትምህርት ቤቱ በውሳኔዎች አሰጣጥ ላይ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደጉ የተማሪዎች ኃላፊነትን የመውሰድና በዲሲፕሊን የመመራት ባህል ዳብሯል። ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤት ካውንስል፣ የህፃናቶች ፓርላማ እና የክፍል ስብሰባዎች ይጠቀሳሉ።

2.2.2 ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን በአመራር ላይ እንዲሳተፉ ለሁሉም ፆታዎች እኩል ዕድል ሰጥቷል። (ምሳሌ ተማሪዎቹ የትምህርት ቤቱን ክለቦች በመምራት)

2.2.3 የሥነ - ተዋልዶ ጤናና ከዚህም ጋር የተያያዙ የርስ በርስ ግንኙነት ሁኔታዎች በሁሉም ክፍል ደረጃዎች የትምህርት ቤቱ ፕሮግራሞች አካል ናቸው።

2.2.4 የተማሪዎች ባህሪያት በተገቢው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በተለያዩ ሁኔታዎች ወይም አውዶች በግልፅ ታይቷል።

2.2.5 በመማሩ ሂደት ተማሪው ሃላፊነት የሚሰማው፣ በራሱ የሚተማመን፣ ነፃነት የሚሰማውና ተቀባይነት እንዳለው የዳሰሳ ጥናቶች አመልክተዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 2.3፦ ለተማሪ የሚደረግ ድጋፍ** (student support)

**ስታንዳርድ 10፦ የትምህርት አካባቢዎች ለሁሉም ተማሪዎች ምቹ፣ የማያሰጉ፣ ደጋፊ እና የተማሪዎችን ፍላጐት የሚያሟሉ በመሆናቸው ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ ሆነዋል።**

2.3.1 በትምህርት ቤት የሚከናወኑ ማናቸውም የትምህርት ሥራዎች ከሁሉም በላይ ቀዳሚ አድርገው የተንቀሳቀሱት የተማሪውን የመማር ፍላጐት ማሟላትና ውጤት ማሻሻል ላይ መሆኑ ተረጋግጧል።

2.3.2 ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚችሉበት እድሉ አላቸው።

2.3.3 ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎቹ የሚያደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ የትምህርት ብክነትን እንዲቀንስ አድርጓል።

2.3.4 ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን ብቃት አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ውጤታቸው ከፍ እንዲልና በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያስችል ስልት በመዘርጋት ሥራ ላይ አውሏል።

2.3.5 ትምህርት ቤቱ ምቹና የማያሰጋ መሆኑን ከት/ቤቱ ማህበረሰብና ከወላጆች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

2.3.6 ትምህርት ቤቱ የመደበው በጀት የተማሪዎችን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚወጣውን ወጭ ያካተተ መሆኑና ለዚህም ተግባር መዋሉ ተረጋግጧል።

2.3.7 የትምህርት ቤቱ የሥነ-ምግባር ደንቦች፦

- ለሰዎች መሰጠት ስለሚገባው አክብሮትና ለንብረቶች ስለሚደረገው ጥንቃቄ፤
- እንደ ሁከት፣ ማግለልና አድልዎ፣ ኃይል መጠቀም፣ ማስፈራራት፣ ተደባዳቢነትና የመሳሰሉት እኩይ ባህርያት ፍጹም ተቀባይነት እንደሌላቸው፤
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት መንገዶችን (procedures)፤
- የትምህርት ቤቱን ሕግና ደንብ የማክበር ግዴታንና ተቀባይነት ያለው (safe) ባህሪይ ማሳየት የሚገባ መሆኑን የሚገልጹ መግለጫዎችን ያካተቱ ናቸው።

**ስታንዳርድ 11፦ የልዩ ፍላጐት ተማሪዎች ዕኩል የመማር ዕድል አላቸው፤ ለውጤት እንዲበቁም በየችሎታቸው መጠን በተደረገላቸው ዕገዛ መሠረት ስኬታማ ሆነዋል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

2.3.8 በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ (CPD) ፕሮግራም ውስጥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተካቷል።

2.3.9 ት/ቤቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራምን ለመምራት እንዲቻል የሰለጠኑ መምህራንና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እና ፋሲሊቲዎች ለማሟላት ጥረት በማድረግ ፕሮግራሙን ተግባራዊ አድርጓል።

2.3.10 የተማሪዎች ልዩ ፍላጐት ተመዝግቦ ተይዟል፤ ፕሮግራሞችን፣ የማስተማር ዘዴዎችንና ማቴሪያሎችን እንደፍላጐታቸው ተስማሚ እንዲሆኑ በማድረግ በችሎታቸው መጠንም ተምረው ውጤታማ ሆነዋል፡፡

2.3.11 ተማሪዎች ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች ስላገኙት የእርካታ ደረጃ በወላጆች ላይ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች ያመለክታሉ።

2.3.12 የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ያለችግር ሊጠቀሙባቸው እንዲችሉ በቀላልና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የተደራጁ ናቸው።

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 3፦ የትምህርት ቤት አመራር

የትምህርት ቤት አመራር ለትምህርት ቤቱ ግልጽ ራዕይ መቅረጽ እና ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ደንቦችን በማውጣት ወደ ራዕዩ መምራት ይኖርበታል። ራዕዩ ተማሪን ማዕከል ያደረገ እና ለመምህራን ትኩረት በመስጠት ተከታታይ መሻሻልን የሚፈልግ ነው። አመራርና አስተዳደር የጋራ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

### ንዑስ ጉዳይ 3.1፦ ስትራተጂካዊ ራዕይ

**ስታንዳርድ 12፦** ትምህርት ቤቱ የጋራ የሆነ ራዕይ አለው። የተነደፉት ግቦች እና አላማዎች በትምህርት ቤቱ የቅድሚያ ትኩረት ጉዳዮች ላይ ተንፀባርቀው የሚጠበቀውን ውጤት አስገኝተዋል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.1.1 የትምህርት ቤቱ ስትራተጂካዊና ዓመታዊ እቅዶች በግለ-ግምገማ ውጤት ላይ ተመስርተው በአሳታፊነት የተዘጋጁ ናቸው።

3.1.2 ከትምህርት ቤቱ ራዕይና ግቦች ጋር ጎን ለጎን የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማ (professional appraisal) እና ሙያዊ ትምህርቶች አሉ።

3.1.3 በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑት ተግባራት በቋሚነትና ሳይዋዥቁ (consistently) የሚተገበሩ መሆናቸው ተረጋግጧል።

3.1.4 እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች (ethics)፣ መሪ የሆኑ መርሆዎችና የትም/ቤቱ ዓላማዎች በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በመላ የታወቁ ናቸው።

3.1.5 የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ እቅድ ለማሳወቅና ለመተግበር የሚያስችሉ ስልቶች በግልፅ ተቀምጠዋል።

3.1.6 የትምህርት ቤቱ አመራር ሰጭ አካላት በግልጽ ስለተቀመጡት ግቦችና ስለሚጠበቁ ከፍተኛ ውጤቶች አዘውትረው ይገልፃሉ፤ የተገኙ መሻሻሎችንም ተከታትለዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 3.2፦ የመሪነት ባህርይ**

**ስታንዳርድ 13፦** ቀጣይነት ያለውና በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ቤት መሻሻል መኖሩ ተረጋግጧል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.2.1 ትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የነደፋቸውን የትምህርት ቤት መሻሻል ቅድሚያ ትኩረቶች ውጤታማነት ለመተንተንና ለማወቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።

3.2.2 በተከታታይ የተመዘገቡ መረጃዎች (Longitudinal Data) የተማሪዎች ውጤቶች መሻሻላቸውን ያንፀባርቃሉ። ይህም በውጭ አካል (External validation) በተደረገው ግምገማ ተረጋግጧል።

**ስታንዳርድ 14፦** ትምህርት ቤቱ የእርስ በርስ ሙያዊ መማማሪያ የሚካሄድበት ተቋም በመሆኑ የመምህራንና የአመራር ሙያዊ ብቃት ተሻሽሏል ።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.2.3 የትምህርት ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን አካቷል።

3.2.4 ለትምህርት ቤቱ መምህራን የተሻለ ልምድ ባላቸው መምህራን ሥልጠና/እገዛ (coaching and mentoring) የሚደረግላቸው ሥርዓት በመዘርጋቱ የመምህራን ሙያዊ ብቅት ተሻሽላል ።

3.2.5 የትምህርት ቤቱ አመራር የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይተዋል፤ እንዲሁም የአመራር አባላቱ በሥልጠና ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ችለዋል።

**ስታንዳርድ 15፡-** የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የርስ በርስ ግንኙነቶች በመተማመንና በሥራ ባልደረባነት (Collegiality) ላይ የተመሠረተ መሆኑ ጤናማ የስራ አካባቢ ፈጥሯል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.2.6 በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል አዎንታዊ፣ ገንቢ፣ ግልጽነት የተሞላበትና በእኩልነት የተመሰረቱ ግንኙነቶች መስፈናቸውን በመምህራንና በተማሪዎች፣ በሠራተኞችና በወላጆች ላይ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች አረጋግጠዋል።

3.2.7 ትምህርት ቤቱ የአሠራርና የግጭት አፈታት ሂደቶችን የሚገልጽ ሙያዊ ደንብ/ህግ አለው።

**ስታንዳርድ 16፡-** ሁሉም ባለድርሻዎች ለተማሪዎች የትምህርት ውጤት ተጠያቂ መሆናቸውን በመቀበል ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.2.8 ፕሮግራሞችና የተገኙ ስታንዳርዶች ዘላቂነት ያላቸው፣ አስተማማኝ የሆኑ፣ መረጋገጥ የሚችሉ እና ተጨባጭ ውጤቶችን የሚያንፀባርቁ ለመሆናቸው የትምህርት ቤቱ አመራርና መምህራን የማረጋገጥ ሙያዊ ኃላፊነት አለባቸው።

3.2.9 የት/ቤቱ አስተዳደር የልዩ ፍላጎት ትምህርት እስትራቴጂን በመተግበር፣ በማስተባበር፣ በመቆጣጠርና በመገምገም ሙያዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል።

3.2.10 በውጭ አካል የትክክለኛነት ማረጋገጫ (External validation) የትምህርት ቤቱ ግለ ግምገማ፣ የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶችና ፕሮሲጀሮች ትክክለኛነት ጥራት ተረጋግጧል።

3.2.11 መምህራን የተማሪዎችን የእድገት (የመሻሻል) ደረጃ ከሚጠበቁ ውጤቶች (Expected outcomes) ጋር በማነፃፀር የሚያዩበት ቋሚ የሆኑ መንገዶች አሏቸው።

**ስታንዳርድ 17፡-** የትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትና አስተዳደራዊ ተግባራት የጋራ ክንውን በመሆናቸው በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል የስራ አንድነት ሰፍኗል፡፡

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.2.12 የወላጅ-መምህር ህብረት (P.T.A)፣ የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች፣ የት/ቤት መሻሻል ኮሚቴና የተማሪዎች ተወካዮች ካውንስል አካላት በትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በመሳተፋቸው የሥራ አንድነት ተፈጥሯል።

3.2.13 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች በግልጽ የተብራሩ፣ በማስረጃ የተደገፉ፣ በቀጣይነት የሚተገበሩ ናቸው፤ የሂደቱ ውጤቶችም ተመዝግበዋል።

## ንዑስ ጉዳይ 3.3፦ የትምህርት ቤት አመራር/አስተዳደር

**ስታንዳርድ 18፦** የትምህርት ቤቱ የሪሶርስ አመራር የትምህርት ፕሮግራሞችንና የትምህርቱን እድገት የሚደግፍ በመሆኑ የአሰራር ውጤታማነት ጎልብቷል።

### የትግበራ ጠቋሚዎች

3.3.1 ትምህርት ቤቱ ከክለስተር ማዕከል እና ከሌሎች የአካባቢው ተቋሞች ሪሶርሶችንና የሠለጠኑ ባለሙያዎችን በመጠቀሙ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሻሽሏል ።

3.3.2 የሰው፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ሪሶርሶች ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸውና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ በሚደግፍ መልኩ (ሁኔታ) ተመርተዋል፣ ጥቅም ላይም ውለዋል።

**ስታንዳርድ 19፦** በት/ቤቱ ውጤታማ ውስጠ ደንብ፣ መመሪያዎችና የአሰራር ሥርዓቶች ተደራጅተው ሥራ ላይ በመዋላቸው የተጠናከረ አሠራር ሰፍኗል።

### የትግበራ ጠቋሚዎች

3.3.3 የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መመሪያዎችን፣ ባህርይንና ዲሲፕሊንን፣ ከፆታና የዘር ዳራ አኳያ እኩል የሆነ የምቹ ዕድሎች አጠቃቀምን ያካተቱ ናቸው።

3.3.4 የትምህርት ቤቱ ውስጠ ደንብ በሰነድነት ተመዝግቦ ተይዟል (documented)፤ እንዲሁም ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተሻሽሎ በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ ውሏል።

3.3.5 የትምህርት ቤቱ ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች፣ ከትምህርት ቤቱ መርሆዎችና እሴቶች ጋር በመጣጣሙ የተጠናከረ አሠራር ሰፍኗል።

**ስታንዳርድ 20፦** በትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር ውጤታማ የሆነ ተግባቦት (communication) መኖሩ በትምህርቱ ሥራ ላይ የባለቤትነት ስሜት አሳድጓል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

3.3.6 ትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር መደበኛና ውጤታማ የሆነ ተግባቦት (communication) በመፍጠሩ የተገልጋይ እርካታን አስገኝቷል።

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 4፦ የህብረተሰብ ተሳትፎ

ጥራት ያለው አጋርነትንና (Partnership) የግንኙነት መረብን ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር መፍጠር ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ከህብረተሰቡ ጋር ለማቀራረብ (ለማገናኘት) ያስችላቸዋል። እውነተኛና ቀጣይነት ያለው አጋርነት ትምህርት ቤቶች ለህብረተሰቡ መረጃዎች ለመስጠትና ህብረተሰቡ ለሚጠብቃቸው ትልሞች (Expectations) ምላሽ ለመስጠት ይረዳቸዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 4.1፦** ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር አብሮ መሥራት (Partnership with parents and careers)

**ስታንዳርድ 21፡- ወላጆችና አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳዮች በንቃት መሳተፋቸው የተማሪዎችን መማር አጐልብቷል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

4.1.1 የወላጆች ተሳትፎን ለመደገፍ የተዘረጉ ተቋማዊ መዋቅሮች አሉ፤ ትምህርት ቤቱ በሚጠራው ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉም ተበረታተዋል ።

4.1.2 ወላጆች የልጆቻቸውን የቤት ሥራ በመመልከት አስተያየት ሰጥተዋል።

4.1.3 በትምህርት ቤቱ በሚካሄዱ ፕሮግራሞችና የመረጃዎች ልውውጥ የወላጆች ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ።

**ስታንዳርድ 22፡- በትምህርት ቤቱና በወላጆች/አሳዳጊዎች መካከል የተፈጠረ ውጤታማ ግንኙነት የተማሪዎች መማርን የሚያበረታታና የሚያግዝ ሆኗል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

4.1.4 የተማሪ ፕሮግራሞችና ውጤቶች ሪፖርት ማድረጊያ መደበኛ የሆነ የጊዜ መርሐ-ግብር አለ።

4.1.5 ወላጆች/አሳዳጊዎች እንደ ወላጅ-መምህር ህብረትና የቀበሌ የትምህርትና የሥልጠና አመራር ቦርድ ባሉ መደበኛ መዋቅሮች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አለ።

4.1.6 የመምህራን መረጃ መዝገቦች መምህራን ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር የተገናኙበትን ድግግሞሽ (Frequency) ከፍተኛ መሆን የተማሪዎች ውጤትና ባሕሪ እንዲሻሻል አድርጓል። የመምህራን መረጃም ትንታኔውን ለይተው ያሳያሉ፡፡

4.1.7 በትምህርት ቤቱ መዝገቦች ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ያደረጉ ወላጆችንና አሳዳጊዎች ተመዝግበው ተይዘዋል፡፡

## ንዑስ ጉዳይ 4.2፡- ኅብረተሰብን ማሳተፍ

**ስታንዳርድ 23፡- ትምህርት ቤቱ ከኅብረተሰቡ እና ከውጫዊ ድርጅቶች (external organizations) ጋር ተባብሮ የመስራት ልምድ በመጠናከሩ ውጤታማ አገርነት ተፈጥሯል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

4.2.1 የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ያካተተ የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ አለ።

4.2.2 ለወላጆችና ለህብረተሰቡ ትምህርት ለመስጠትና ሌሎች ድጋፎች/ማንበብና መፃፍን ማስተማር፣ ጐጂ ልምዶችን ማስወገድ፣ ልማት ነክ ተግባራትን ማከናወን ወዘተ/ ለማድረግ ት/ቤቱ ፕሮግራም በማውጣት ተግባራዊ በማድረጉ ውጤታማ አጋርነት ተፈጥሯል።

4.2.3 በርካታ ውጫዊ ድርጅቶች ለመማር-ማስተማሩ ሥራ ልምዶቻቸውን በማካፈል ድጋፍ ሰጥተዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 4.3፡-** የትምህርቱን ሥራ ማስተዋወቅ (Promoting Education)

**ስታንዳርድ 24፡-** የትምህርት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በመልካምነታቸውና በጠቃሚነታቸው ለውጭው ኀብረተሰብ የማስተዋወቅ ሥራ በመሠራቱ በትምህርት ቤቱ ሥራ ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ ዳብሯል፤ ድጋፍም ጨምሯል።

**ትግበራ ጠቋሚዎች**

4.3.1 ትምህርት ቤቱ ስላከናወናቸው ወቅታዊ ተግባራት መስኀብነት ባለው ስልት /በትምህርት ቤት ጋዜጣ፣ በበራሪ ፁሁፍ፣ በስብሰባ ወዘተ/ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለውጭው ህብረተሰብ በስፋት በማሰተዋወቁ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ዳብሯል።

4.3.2 የትምህርት ቤቱ ስኬታማ ክንውኖች በትምህርት ቤት አከባበር ተደርጎላቸዋል።

# ተቀጽላ -1
# የትምህርት ቤት መሻሻል
# የግለ-ግምገማ ፎርም

ትምህርት ቤቶች የመሻሻል ፕሮግራሞቻቸውን በዕቅድ ላይ ተመሰርተው በተግባር ለማዋል የሚችሉት፤ ከሁሉ አስቀድሞ በአራቱ አቢይ ርዕስ ጉዳዮች (Domains) አንጻር ተጨባጭ እና አስተማማኝ በሆነ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ያሉበትን ደረጃ ሲያውቁና የመሻሻል ዕቅድ አውጥተው ወደ ተግባር ሲገቡ ብቻ ነው። ደረጃቸውን ለማወቅም የደረጃ መስፈርት (Rating scale) ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ሰነድ በሁሉም አበይት የት/ቤት ርዕሰ ጉዳዮች ሥር ለተቀመጡት ስታንዳርዶች ደረጃቸውን ለመወሰን ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ በተዘረዘሩት የትግበራ ጠቋሚዎች አንጻር ት/ቤቶቹ ደረጃቸውን ለመወሰን የሚረዷቸው መስፈርቶች ከነመገለጫዎቻቸው (Descriptors) በዝርዝር ቀርበዋል።

ት/ቤቶች በሚሰበስቡት መረጃ መሰረት ከየትግበራ ጠቋሚዎቹ ትይዩ የሰፈሩትን የባህርዩን ደረጃ የሚያመላክቱ መገለጫዎች (Descriptors) በመመልከት ደረጃውን ይወስናሉ። ደረጃውን ሲወስኑም ለመወሰን ያስቻሏቸው ማስረጃዎች (Evidence) ሊኖራቸው ይገባል። እነዚህ ማስረጃዎች ከዳሰሳ ጥናት፣ ከዶክመንት፣ ከምልከታ ወዘተ የሚገኙ ናቸው። በመጨረሻም ከዚህ በታች የቀረቡትን ማሳሰቢያዎች ሁሉም ትምህርት ቤቶች ተገንዝበው ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

1. በእያንዳንዱ የትግበራ ጠቋሚ አንፃር የተቀመጡት ሁሉም የደረጃ መገለጫዎች (Descriptors) መሰረት የሚያደርጉት አጠቃላይ የደረጃ መስፈርቱን ነው። አጠቃላይ የደረጃ መስፈርቱ ለሌሎቹ እንደ ማጣቀሻ (Reference) ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ሲሆን፤ በየትግበራ ጠቋሚዎቹ አንጻር የተቀመጡት ግን እንደ ጠቋሚዎች ባህርይ የሚለዋወጡ ናቸው። ሆኖም የዋናውን ማጣቀሻ መሰረታዊ የደረጃ መለኪያ እርከን የሚያፋልሱ እንዳይሆኑ ጥረት ተደርጓል።
2. በየትግበራ ጠቋሚዎቹ አንፃር ያሉት የደረጃ መገለጫዎች ግልጽ ካልሆኑ፤ ሊለኩ የማይችሉ ወይም ከትም/ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይስማሙ ናቸው ተብሎ በኮሚቴው ከታመነበት ሊለወጡ፣ ሊሻሻሉ ይችላሉ። ሆኖም የተሻሻሉት ወይም የተለወጡት የደረጃ መገለጫዎች የትግበራ ጠቋሚውን ባህርይ ጠብቆ በዋናው የደረጃ መሰፈርት መገለጫዎች መሰረት መሆን ይኖርባቸዋል።
3. የተደረጉት ማንኛውም ዓይነት ለውጦች ወይም ማሻሻያዎች፣ ለውጥ ወይም ማሻሻያ የተደረገባቸውን መገለጫዎች ስላለባቸው ችግር በመግለጽ ከነማስተካካያ ኃሳቡ ት/ቤቱ በሚገኝበት የወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤት የት/ቤት መሻሻል ኮሚቴ አማካኝነት ለክልሉ የት/ቤት መሻሻል ፕሮግራም ማስተባባሪያ መላክ ይኖርባቸዋል።

## ለሁሉም አቢይ ርዕስ ጉዳዮች የሚያገለግል የደረጃ መስፈርት (Rating Scale)

| | |
|---|---|
| **4፡ የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ** | ትምህርት ቤቱ ለማሻሻያው በደንብ የታሰበበት በሁሉም ባላድርሻዎች ተቀባይነት ያለው ዕቅድ አለው። ዘላቂ እና አስተማማኝ መሰረት ያላቸው (Well established) ውጤታማ ስልቶች እንዳሉት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች አሉት። ሁሉም ባለድርሻዎች በተሳተፉበት አዳዲስ አላማዎችን ለመንደፍ እቅዶች በየጊዜው እየተፈተሹ ይከለሳሉ፣ ይገመገማሉ። ስትራተጂዎች ዘልቀው ወርደዋል፣ የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ዘላቂነት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጡ አስረጂዎች (ማስረጃዎች) በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። (የተጠቀሰውን ባህርይ አስመልክቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የተደረገ ዳሰሳ ጥናት **<u>በጣም ከፍተኛ</u>** መሆኑን ያሳያል።) |
| **3፡ በመሥራት ላይ ያለ** | ት/ቤቱ የተጠቀሰውን ባህርይ ጠንካራና መሻሻል የሚገባውን በመለየት የማሻሻያ ዕቅድ ባወጣው እና በነደፈው ስልት መሰረት፣ በርካታ ሥራዎችን ለማከናወኑ ማስረጃ አለው። (ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የተደረገ የዳሳሳ ጥናት **<u>ከፍተኛ</u>** መሆኑን ያሳያል።) |
| **2፡ በመጀመር ላይ ያለ** | ትምህርት ቤቱ የተጠቀሰውን ባህርይ ጠንካራ እና መሻሻል የሚገባውን በመለየት ዕቅድ ለማውጣቱ እና የትግበራ ስልት ለመንደፉ ማስረጃ አለው። የመሻሻል ርምጃ ለማድረግ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ጀምሯል። (ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የተደረገ የዳሰሳ ጥናት **<u>መጠነኛ</u>** መሆኑን ያሳያል።) |
| **1፡ በዝግጅት ላይ ያለ** | ትምህርት ቤቱ መሻሻል የሚገባውን ጉዳይ ለይቶ ማስቀመጥ ለመጀመሩ ማስረጃዎች አሉት። ነገር ግን የማሻሻያ ዕቅድ ገና አላወጣም። (ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የተደረገ የዳሰሳ ጥናት **<u>ዝቅተኛ</u>** መሆኑን ያሳያል።) |
| **ተጨባጭ ያልሆነ / የሚታይ ተግባር የሌለው** | ትምህርት ቤቱ ስለማሻሻያ መስኮች ወይም መሻሻል ስለሚገባቸው ነገሮች ገና ማሰብ አልጀመረም። የት/ቤቱ ማህበረሰብም ስለተጠቀሰው ባህርይ የክንውን ደረጃ ለማወቅ እርግጠኛ መሆን የሚያስችለው አስተማማኝ መረጃ የለውም። |

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 1፦ መማርና ማስተማር

**ንዑስ ጉዳይ 1.1፦ የማስተማር ተግባር**

**ስታንዳርድ 1፦ የመምህራን እውቀትና እሴቶች በተለያዩ ሥልጠናዎች አድገው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.1.1 | ት/ቤቱ ጥራት ላለው መማርና ማስተማር ጠንካራ መሠረት የሚጥሉ በጋራ የተዘጋጁ እሴቶች አሉት። | ት/ቤቱ ዘላቂ እና ጠንካራ መሰረት ያላቸው (well-established) ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በጋራ የተዘጋጁ እሴቶች አሉት። | ት/ቤቱ ከመምህራን ጋር በመሆን ያዘጋጀው እሴቶች አሉት። ለወደፊትም ለት/ቤቱ ማህበረሰብ በሙሉ ለማካፈል በዕቅድ ይዟል። | ት/ቤቱ እሴቶች አሉት፣ ነገር ግን የት/ቤቱ ማህበረሰብን በማማከር ወይም በጋራ የተዘጋጁ አይደሉም። | ት/ቤቱ የእሴቶች ስብስብ ሊኖረው እንደሚገባ ያውቃል። ሆኖም እስካሁን አላዘጋጀም። | |
| 1.1.2 | መምህራን ተማሪዎቻቸው የተለያየ የመማር ፍጥነት እንዳላቸው በመቀበል የማስተማር ዘዴዎቻቸውን በዚሁ መሠረት አስተካክለው በመጠቀም የተማሪዎች ውጤት ተሻሽላል። | መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን የመማር ፍጥነት በመለየት አቅደው በተግባር በማዋላቸው የተማሪዎች ውጤት ተሻሽለዋል፡፡ ይህንኑ የሚያረጋግጡ ዘላቂና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎች ት/ቤቱ አሉት። | በታቀደው ዕቅድ መሠረት መምህራን የተማሪዎቹን የመማር ፍጥነት ልዩነት መረዳት የሚችሉበትን ስልት በተግባር ማዋል ጀምረዋል። መምህራን የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎቶች ለይተው ለማስተማር የሚያስችላቸውን ዕቅድ አውጥተው መተግባር ጀምረዋል። | መምህራን የተማሪዎችን የተለያዩ የመማር ፍጥነት ለይተው አንዲያስተምሩ ለማስቻል የሥልጠና እና አመራር የመስጠት ዕቅድ አውጥቷል። | ት/ቤቱ የተለያዩ ተማሪዎችን የመማር ፍጥነት በመለየት እንደየፍላጐታቸው የማስተማር ዘዴ በመቀየስ መማር እንዳለባቸውና ውጤታቸውን ማሻሻል እንዳለባቸው ያውቃል። ሆኖም በዚህ ረገድ እስካሁን ያደረገው እንቅስቃሴ የለም። | |
| 1.1.3 | መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ማብራሪያዎችና መግለጫዎች ቀላልና ግልጽ ናቸው። | የት/ቤቱ መምህራን በሙሉ ለተማሪዎቻቸው ግልፅ የሆኑ ማብራሪያዎችና መግለጫዎች መስጠት የዘወትር ተግባራቸው ለመሆኑ ት/ቤቱ በመረጃ ያረጋግጣል። | ት/ቤቱ በቀየሰው ስልት መሠረት አብዛኛው መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ማብራሪያዎችና መግለጫዎች ግልፅ ለመሆናቸው ማረጋገጫ አለው። | መምህራን የሚሰጧቸው መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ግልፅ መሆን ያለባቸው መሆኑን ት/ቤቱ አምኖ የመከታተያ ስልት ቀይሷል። | መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ማብራሪያዎች ግልፅ መሆን እንዳለባቸው ት/ቤቱ ያምናል። ሆኖም በምን መልክ በተግባር ላይ እንደሚውል ማረጋገጫ መንገድ አልቀየሰም። | |
| 1.1.4 | መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ተምሳሌት ናቸው፣ ለተማሪዎቻቸው አስፈላጊውን ከበሬታ ስለሚሰጧቸው ተማሪዎቻቸው የደህንነትና በራስ የመተማመን ስሜት አድሮባቸዋል። | በጣም ጥሩ የሆነ የመማር ሁኔታና የርስ በርስ መከባበር ስሜት ዳብሯል። በትምህርት ቤቱ የተረጋጋ የመማር ሁኔታና አካባቢ (learning environment) ተፈጥሯል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | የርስ በርስ ግንኙነቶች በዋነኛነት በጥሩ ደረጃ ላይ ናቸው ትምህርት ቤቱ ጥሩ ባህርይ እና መከባበር እንዲኖር ስልት ነድፎ ለማሻሻል ጥረት አድርጓል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ከፍተኛ ነው። | ትምህርት ቤቱ ርስ በርስ መከባበር ላይ የተመሠረተ ስልት ነድፎ ለማሻሻል አቅዶአል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ መጠነኛ መሆኑን ያሳያል። | የመምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት በተደረገው ዳሰሳ ጥናት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | | | | | | |
| 1.1.5 | መምህራን ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመው ቀደም ብለው ለይተው በማወቅ ድጋፍ በመስጠታቸው የትምህርት አቀባበላቸው ተሻሽሏል። | ት/ቤቱ ለአካቶ ትምህርት አተገባበር አስተማማኝ መሠረት ጥሏል። የተለያዩ የመማር ፍላጐቶችም ተለይተው ድጋፍ በመደረጉ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበላቸው በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል፡፡ (የዚህ ማረጋገጫው የክትትል መዝገቦችና የተማሪዎቹ ውጤቶች ይሆናሉ) | ትምህርት ቤቱ ለአካቶ ትምህርት አተገባበር መሠረት ለመጣል የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች አከናውነዋል። ይህንን የሥልጠናና የክትትል መዝገቦች ያረጋግጣሉ። | ት/ቤቱ የልዩ ፍላጐት ተማሪዎችን መለየትና ማገዝ የመምህራን የሥራቸው አካል እንዲሆን የሚያስችል እቅድ አዘጋጅቷል። | ት/ቤቱ ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት እገዛ ማድረግ እንደሚገባ ቢያውቅም እስካሁን ምንም እቅድ አላወጣም። | |
| 1.1.6 | መምህራን በልዩ ፍላጐት፣ በፆታ፣ በሃይማኖትና በዘር ላይ በመመሥረት አንዳችም ልዩነት ሳያደርጉ የሁሉንም ተማሪዎች መብት በዕኩልነት ያከብራሉ፣ ተገቢውንም ድጋፍ ይሰጣሉ። | ለተማሪዎቹ ዕገዛ ማድረግ እና መብታቸውን ማክበር ያለአድልዎ መሆን እንዳለበት በት/ቤቱ እሴቶችና እምነቶች አካል ሆኖ ተወስዷል። በተማሪዎች ላይ በተደረገው የዳሰሳ ጥናትም አተገባበሩም በሁሉም መምህራን ዘንድ "በጣም ከፍተኛ" እንደሆነ ያሳያል። | ለተማሪዎቹ ዕገዛ ማድረግ እና መብታቸውን ማክበር ያለአድልዎ መሆን እንዳለበት በት/ቤቱ እሴቶችና እምነቶች ስብስብ ውስጥ ተካቷል። ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ አተገባበሩም በመምህራን ዘንድ ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል። | ት/ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች ያለአድልዎ በእኩልነት የተማሪዎችን መብት የሚያከብሩበትንና አስፈላጊውን እገዛ የሚያደርጉበትን መንገድ ለማጠናከር ሁኔታዎችን መልሶ እየመረመረ ነው። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ መጠነኛ እንደሆነ ያሳያል። | ትምህርት ቤቱ ያለአድሎ የተማሪዎችን መብት ማክበር እንዳለበት ያውቃል። ወደፊት በትምህርት ቤቱ እሴቶችና እምነቶች ውስጥ ለማካተት ያስባል። ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ አተገባበሩ ዝቅተኛ እንደሆነ ያመላክታል። | |
| 1.1.7 | መምህራን ለተከታታይ የሙያ መሻሻል መሠረት የሚሆናቸውን እንደተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም (CPD)፣ የርስ በርስ ልምድ ልውውጦች አጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠናዎችንና ሌሎች ለሙያ ማሻሻያ ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችንና መዋቅሮችን በመጠቀም የማስተማር | በት/ቤቱ የመምህራንን የሥልጠና ፍላጐት በመለየት ከት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ጋር የተጣጣመ የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ዕቅድ አውጥቶ እንዲተገበር ማድረግ ባሕል ሆኗል ። መምህራን የሙያ ዕውቀታቸውንና ክሂሎትን በሚያሳድጉ ሥልጠናዎች ላይ እንዲገኙ ት/ቤቱ ድጋፍ ያደርጋል። (የዚህ ማረጋገጫ የት/ቤት | ት/ቤቱ የመምህራንን የሥልጠና ፍላጐት ከት/ቤት መሻሻል ፕሮግራም ፍላጐቶች ጋር ተጣጥሞ እንዲካሄድ መምህራን የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ እየሰጠ ነው።(የዚህ ማረጋገጫ የሥልጠና መዝገቦችና የCDP ዕቅዶች ሊሆኑ ይችላሉ) | ጥቂት መምህራን የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ይከታተላሉ፤ ነገር ግን የኮርስ ምርጫው በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ላይ ተመስርቶ አይደለም። ሆኖም ለወደፊቱ ት/ቤቱ መምህራን የሥልጠና ፍላጐታቸውን እንዲለዩ እና | መምህራን የተከታታይ የሙያ ዕድገት (CDP) ዕቅድ በግል የላቸውም። ጥቂት መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርሶችን ይከታተላሉ። ነገር ግን የኮርስ ምርጫው በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ላይ ተመስርቶ አይደለም። ት/ቤቱ ይህን በተመለከተ ዕቅድ ለማውጣት እየተዘጋጀ ነው። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ብቃታቸውን አሻሽለዋል። | መሻሻል ዕቅዶች፣ የሥልጠና መዝገቦችና የCDP ዕቅዶች ትግበራ ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ) | | የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ዕቅድ እንዲያወጡ የሚያስችል ዕቅድ አውጥቷል። | | |
| 1.1.8 | መምህራን ሥራዎቻቸውን መልሶ ለመመርመርና ለማጥራት ከባለድርሻዎች የተሰጧቸውን የሰሉ (critical) አስተያየቶች ተጠቅመው አፈጻጸማቸውን አሳድገዋል፣ | የት/ቤቱ መምህራን የሚሰጧቸውን አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ለእርምት ሂደቱ እቅድ በማውጣት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ማረጋገጫም ከተማሪዎች፣ ከዲፖርትሜንት ኃላፊዎች ከር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሚገኙ መረጃዎች፣ | የት/ቤቱ መምህራን በሚሰጣቸው አስተያየት መሠረት ለእርምት ሂደቱ እቅድ በማውጣት አብዛኛው ተግባራዊ አድርገዋል፣ | የት/ቤቱ መምህራን በሚሰጣቸው አስተያየት መሠረት እርማት ለመውሰድ እቅድ አዘጋጅተዋል። | የት/ቤቱ መም/በሚ ቀርብላቸው አስተያየት መሠረት ማሻሻል ያለ ባቸው መሆኑን ተገን ዝበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ስልት አልቀየሱም፣ | |
| 1.1.9 | የትምህርት ቤቱ መምህራን በሚያወጡት ዓመታዊና ዕለታዊ እቅዳቸው መሰረት ማስተማራቸው ተረጋግጧል። | መምህራን ዓመታዊና ዕለታዊ ዕቅዳቸውን አውጥተውና አጣጥመው ማስተማር የቆየ ባህላቸው አድርገውታል። በተለያዩ ምክንያቶች በዕቅድ መሰረት ያልተከናወኑ ተግባራት ምክንያታቸው ተገልጾ ማስተካከያ ያደርጋሉ። ትምህርት ቤቱም ይህንኑ የሚከታተልበት ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ ስልት አለው። | መምህራኑ ዓመታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ እንዳላቸው መከታተያ ስልት ትምህርት ቤቱ አለው። በዚህም መሰረትአብዛኛው መምህራን በዕቅዳቸው መሰረት ያስተምራሉ ። ትም/ቤቱ በቀየሰው ስልት መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች በዕቅድ መሰረት ያልተከናወኑ ተግባራት ምክንያታቸው ተገልጾ ማስተካከያ ማድረጋቸውን መከታተል ጀምሯል። | መምህራኑ ዓመታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ እንዳላቸው መከታተያ ስልት ትምህርት ቤቱ አለው። በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች በዕቅድ መሰረት ያልተከናወኑ ተግባራት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት ቀይሷል። | መምህራኑ ዓመታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ እንዳላቸው መከታተያ ስልት ትምህርት ቤቱ አለው። ሆኖም በዕቅዳቸው መሰረት የሚያስተምሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ስልት ገና አልቀየሰም። | |
| 1.1.10 | መምህራን ከተማሪዎቹ፣ ከመማር አውዱ (Learning context) ፣ ከትምህርት ይዘት ከተፈላጊው ዓላማና ውጤት አኳያ ተገቢነት | በት/ቤቱ ተገቢ የሆኑ የማስተማር ዘዴዎች ከትምህርቱ ዓላማና ይዘት፣ ከመማር 0ውድ፣ ከተማሪዎቹ የመማር ፍላጐት አኳያ መምህራን እያጣጣሙ | መምህራኑ የትምህርት ዕቅዳቸውን ሲነድፉ የማስተማር ዘዴዎችን ከትምህርቱ ዓላማና ይዘት፣ ከመማር 0ውድ፣ ከተማሪዎቹ የመማር ፍላጐት አኳያ ነው።ይህንንም በተግባር | በት/ቤቱ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አለ። መምህራኑ ትምህርቱን ከዓላማና ይዘት፣ ከመማር ዐውድ እና በተማሪዎቹ | በት/ቤቱ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አለ። ሆኖም በዕቅድ ዘግጅቱ ላይ መምህራኑ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ከትምህርት ዓላማ፣ ከመማር | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ያላቸውን የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና ስትራተጂዎችን ተጠቅመው በማስተማራቸው ተማሪዎች ረክተዋል። | ማቀድና መተግበር የተለመደ የዘውትር ተግባር ሆኗል። ት/ቤቱም እየተከታተለ ሂደቱን የሚያሻሽልበት ስልት አለው። በዳሰሳ ጥናት በተገኘ መረጃ እና በተለያዩ ሰነዶች የተማሪዎችን እርካታ ማረጋገጥ ተችሏል። | ላይ ማዋል ጀምረዋል። ት/ቤቱም በክትትል ዕቅዱ መሠረት እየተቆጣጠረ ያበረታታል። ለዚህም የተማሪዎች እርካታና የተለያዩ ሰነዶች ያስረዳሉ። | ፍላጎት ላይ በመመሥረት የማስተማር ዘዴያቸውን በዕቅዳቸው ላይ እንዲያሠፍሩ ማበረታታት ጀምሯል። የክትትል ዕቅድም አውጥቷል። | አውድና ከተማሪዎቹ ፍላጎት አኳያ፣ ዘዴዎችን የሚያስተምሩበትን ሁኔታ አያመለክቱም። ት/ቤቱ ይህ እንደሚያስፈልግ ያውቃል። | |
| 1.1.11 | መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ጥሩ እውቀት አላቸው፤ ይህንንም እውቀታቸውን በክፍል ውስጥ በብቃት ተግባራዊ በማድረግ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል የተሻለ ሆኗል፡፡ | የትምህርት ቤቱ መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ጥሩ እውቀት ስላላቸው የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል፡፡<br>የዚህ ማረጋገጫው የመምህራኑ የክትትል መዝገቦች ናቸው፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ | ትምህርት ቤቱ መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት እውቀት እንዳላቸው ያምናል፡፡ በዚህም የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል፡፡ የዚህ ማረጋገጫው የመምህራኑ የክትትል መዝገቦች ናቸው፡፡ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ | ትምህርት ቤቱ ከመምህራኑ ውስጥ የሚያስተምሩትን ትምህርት ልበ ሙሉ ሆነው የማያስተምሩ እንዳሉ ያውቃል፡፡ ይኸንን እንዴት እንደሚያሻሽሉ ስልት ቀይሳል፡፡ እቅድም አውጥቷል፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ አጥጋቢ መሆኑን ያሳያል፡፡ | ትምህርት ቤቱ ከመምህራኑ ውስጥ የሚያስተምሩትን ትምህርት ልበ ሙሉ ሆነው የማያስተምሩ እንዳሉ ያውቃል። ይህንን እንዴት እንደሚያሻሽሉ ገና ስልት አልቀየሰም፣ ዕቅድም አላወጣም። ከተማሪዎች የተገኘው መረጀ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። | |

**ስታንዳርድ 2፡-** መምህራን ያላቸውን ሙያዊ እውቀት በሚገባ በመጠቀም፣ በፍላጎታቸውና በቁርጠኝነት መሥራት እንዲሁም ከተማሪዎቻቸው ብዙ በመጠበቅ ( High expectations) ለማስተማር ተግባሩ መሠረት በማድረግ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.1.12 | የመምህራን የማስተማር ተግባር ለማዳበር (ለማጐልበት) የሚረዱ ወቅታዊ ጥናትና ምርምርን መሠረት ያደረጉ መንገዶች | በት/ቤቱ አስተማማኝ መሠረት ላይ ያሉ (well established) የመምህራን የማስተማር ተግባር ለማጐልበት የሚረዱ መንገዶች አሉ። በዚህም፣ በመምህራኑ ዘንድ የጋራ | ት/ቤቱ ባወጣው ፕሮግራም መሠረት የተወሰኑ የሙያ ማሻሻያ የውይይትና የመማማሪያ ፕሮግራሞች ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት ት/ቤቱ የማስተማሩን | መምህራን ሥራቸውን መልሶ መመርመርና መገምገም እንዳለባቸው ት/ቤቱ ቢጠብቅም እስካሁን የጋራ የሆነ አመለካከትና የግምገማ | ት/ቤቱ መምህራን ሥራቸውን መልሶ በመመርመር እና በመገምገም የወደፊቱን የትምህርት | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | (Procedures) አሉ። | መግባባትና አመለካከት ዳብሯል። ት/ቤቱም መምህራን ሥራቸውን በጥልቀት የሚመረምሩበትን አጋጣሚዎች ሁሉ በመጠቀም የማስተማሩ ሥራ እንዲጐለብት አድርጓል፡፡ (የዚህ ማረጋገጫው፣ የመምህራን የትምህርት ዕቅድ፣ የግምገማ እና የክትትል መዝገብ ናቸው) | ሥራ በመከታተል መምህራን ሥራቸውን መልሰው በመመርመር የወደፊቱን እንደሚያቅዱ እያረጋገጠ ይገኛል።(የዚህ ማረጋገጫው፣ የመምህራን የትምህርት ዕቅድ፣ የግምገማ እና የክትትል መዝገብ ናቸው) | ተግባር አልዳበረም። ሆኖም ከክትትልና በተግባር ላይ ከታየው በመነሳት ወቅታዊ የሆኑ የማስተማር ዘዴዎች ላይ ሥልጠናና የውይይት ፕሮግራሞች ለማካሄድ አቅዷል። | ዕቅዳቸውን እንዲያዘጋጁ ማበረታታት እንዳለበት ያውቃል። ሆኖም ይህን ለማድረግ ምንም ዘዴ አልቀየሰም። | |
| 1.1.13 | መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤት ለማሻሻል አቅደው በመንቀሳቀሳቸው የተቀመጠውን ግብ አሳክተዋል። | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን የተዘረጋውን አሰራር ሥርዓት ተጠቅመው ያቀዱትን ውጤት ግብ አሳክተዋል። ለዚህም የትምህርት ቤቱ አገር አቀፍና ክልል አቀፍ ፈተና ውጤቶች ያረጋግጣሉ። | አብዛኛው የትምህርት ቤቱ መምህራን የተዘረጋውን አሰራር ሥርዓት ተጠቅመው ያቀዱትን ውጤት ግብ አሳክተዋል። ለዚህም የትምህርት ቤቱ አገር አቀፍና ክልል አቀፍ ፈተና ውጤቶች ያረጋግጣሉ። | ከፊሉ የትምህርት ቤቱ መምህራን ያቀዱትን ውጤት ግብ አሳክተዋል። የትምህርት ቤቱ ውጤት ትንተናም ይህንኑ ያረጋግጣል። | ጥቂት መምህራን በራሳቸው ተነሳሽነት ውጤት ያሻሻሉ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ያሰራር ሥርዓትና ዕቅድ የለውም። በቀጣይ ይህንን መስራት እንዳለባቸው አምነዋል። | |
| 1.1.14 | መምህራን እየተካሄደ ላለው የሙያ ማሻሻያ ትምህርት ያላቸው ቁርጠኝነት በንቁ ተሳትፏቸው አረጋግጠዋል፡፡ | በትምህርት ቤቱ ዘላቂ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ የመምህራንን የሥልጠና ፍላጐት መለየት የሚያስችልና ሥልጠናውም ከትምህርት ቤት መሻሻል ዓላማ ጋር የተያያዘ እንዲሆን የሚያደርግ ሥርዓት አለ። በዚህም ሁሉም የት/ቤቱ መምህራን በንቃት በመሳተፍ የሙያ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን አሳድገዋል። (የዚህ ማረጋገጫው የሥልጠና ተሣትፎ | ትምህርት ቤቱ የመምህራን የስልጠና ፍላጐት በማወቅ የቅርብ ክትትል በማድረና በተመቻቸው መርሀ ግብር አብዛኛው መምህራን በፕሮግራሙ በንቃት በመሳተፍ የሙያ እውቀታቸውንና ክህሎቶቻቸውን አዳብረዋል። (የዚህ ማረጋገጫው የሥልጠና መዝገቦችና የCPD ዕቅዶችና ትግበራ ሰነዶች ናቸው)። | ት/ቤቱ የመምህራኑን የሥልጠና ፍላጐት ለማወቅ እና ከት/ቤት መሻሻል ዓላማ ጋር ለማዛመድ የማስተማር ተግባራቸውን በመመርመር ላይ ይገኛል። | ጥቂት መምህራን በሙያ ትምህርት ዕድሎች ተጠቃሚዎች ናቸው። ነገር ግን ይህ በት/ቤቱ ዕቅድ ላይ የተመሠረተ አይደለም። በተጨማሪም የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ የሙያ ማሻሻያ ጉዳይ አልተካተተም። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ትግባር የሌለው |
| | | መዝገቦችና የCPD ዕቅዶች ትግበራ ሰነዶች ናቸው)። | | | | |

## ስታንዳርድ 3፦ መምህራን ተማሪዎችን ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማገናኘት እንዲመራመሩ በማድረጋቸው የመማር ማስተማሩ ሥራ ተጨባጭ ሆኗል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ትግባር የሌለው |
| 1.1.15 | መምህራን ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ በሚያስችላቸው ህብረ ተሰብን መሠረት ባደረጉ ፕሮግራሞችና በትምህርት ቤት ክለቦች እንዲሳተፉ አድርገዋቸዋል። | በት/ቤቱ መቋቋም የሚገባቸው ክበቦች እና ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረጉ ፕሮግራሞች ተደራጅተው በሚገባ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። ት/ቤቱ ተማሪዎቹን በፕሮግራሞቹ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዘወትር ያበረታታል። (በተማሪዎች ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት በጣም ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ እና አዘውትሮ መገኘት እንዳለ ያመለክታል) | በት/ቤቱ በርካታ ክበቦች አሉ። የተደራጁት ክበቦች በተነደፈው ስልት መሠረት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረዋል፤ በተወሰኑ ኅብረተሰቡን መሠረት ባደረጉ ፕሮግራሞችም ተሳትፎ አድርገዋል። በተጨማሪም ት/ቤቱ ሰፋ ባሉ ጉዳዮች የተማሪዎችን ግንዛቤ ሊያሳድግ በሚችሉ ፕሮግራሞች የበለጠ እንዲሳተፉ ዕቅድ አውጥቷል። (በተማሪዎች ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ እና አዘውትሮ መገኘት እንዳለ ያመለክታል) | በት/ቤት ጥቂት ክበቦች ተደራጅተዋል፣ ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረጉ ፕሮግራሞችም ተለይተው ታውቀው ስልቶች ተነድፈዋል። | በት/ቤቱ ክበቦች እና ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረጉ ፕሮግራሞች እንደሚያስፈልጉ ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አላሳዩም። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.1.16 | መምህራን የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎቻቸው ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮቻቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አድርገዋል፣ | ሁሉም የትምህርት ቤት መምህራን የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎች ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮአቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አቅደው ተግባራዊ አድርገዋል። በዚህም መምህራንና ወላጆች ላይ የተደረገ ዳሰሳ ጥናት ከፍተኛ አፈፃፀም ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። | አብዛኛው የትምህርት ቤት መምህራን የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎች ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮአቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አቅደው ተግባራዊ አድርገዋል። በዚህም መምህራንና ወላጆች ላይ የተደረገ ዳሰሳ ጥናት አጥጋቢ አፈፃፀም ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። | የትምህርት ቤቱ መምህራን ተማሪዎች የክፍል ትምህርቱን ከህይወት ተሞክሮቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ማበረታታት ጀምረዋል። | የት/ቤቱ መምህራን የክፍል ትምህርቱን ከተማሪዎች የህይወት ተሞክሮዎች ጋር ማዛመድ እንዳለባቸው ቢያምኑም በተጨባጭ አቅዶ የተሰራ ሥራ የለም። | |

**ንዑስ ጉዳይ 1.2፦ መማርና ግምገማ**

**ስታንዳርድ 4፦ ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች የላቀ ውጤት መምጣት ከፍተኛ ግምት በመስጠቱ ለውጤት መሻሻል መሰረት ሆኗል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.2.1 | የደረጃ ማነፃፀሪያ ነጥቦች (Benchmarks) በግልጽ ተለይተው ተቀምጠዋል። ይህም በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በሙሉ እንዲታወቅ በመደረጉ ለግቦች መሳካት የበኩላቸውን ድርሻ አበርክተዋል፡፡ | ት/ቤቱ አስተማማኝ መረጃ ላይ ተመስርቶ ተጨባጭ (realistic) የሆነና በግልፅ ውይይትና ምክክር የተቀመጡ ተፈታታኝ፣ (Challenging) ግን ሊደረስባቸው የሚችሉ የደረጃ ማጣቀሻ ነጥቦች አሉት። ሁሉም የትም/ቤቱ ማህበረሰብ አባላት ለወጡት ስታንዳርዶች ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ እያበረከቱ ነው። ይህም የትምህርት ቤቱ ሰነድ በማየት ተረጋግጧል። | ት/ቤቱ የደረጃ ማጣቀሻ ነጥቦች አሉት። ይህንኑ ለአብዛኛው ለት/ቤቱ ማህበረሰብ አሳውቆ በመተግበር ላይ ይገኛል። | ት/ቤቱ የደረጃ ማጣቀሻ ነጥቦች አሉት።ይህንኑ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በከፊል በማሳወቅ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል። | ት/ቤቱ የደረጃ ማጣቀሻ ነጥቦች የሉትም። ለወደፊቱ እንደሚያስፈልገው ግን ያውቃል። | |
| 1.2.2 | የተማሪዎች ውጤት መረጃ ቀደም ሲል ከነበረው የመነሻ | ት/ቤቱ ቀልጣፋና ቋሚ የሆነ የመረጃ አሰባሰብና ትንትና ዘዴ | ት/ቤቱ ባወጣው ዕቅድና በተቀየሰው | የተማሪዎች ውጤት ለውጥ (መሻሻል) | ት/ቤቱ የተማሪዎችን | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ነጥብ (ውጤት) የተሻሻለ መሆኑን በግልፅ አሳይቷል። | ስላለው የተማሪዎች ውጤት መሻሻልን በየጊዜው ለመከታተል ችሏል። በዚህም የሁሉም ተማሪዎች ውጤት ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። (ማረጋገጫው ክትትልና ግምገማ መዝገብ ይሆናል) | ስልት መሠረት የተማሪዎችን የውጤት መሻሻል ለመከታተል መረጃ መሰብሰብና መተንተን ጀምሯል። በዚህም አብዛኛው የተማሪዎቹ ውጤት ከአጥጋቢ በላይ ሆኗል። (ማረጋገጫው ክትትልና ግምገማ መዝገብ ይሆናል) | ማሳየቱን ለማወቅ ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ስልት ቀይሷል ዕቅድም አውጥቷል። | ውጤት በተመለከተ የመረጃ ትንተና የሚያደርግበት ዘዴ ገና አልቀየሰም። | |
| 1.2.3 | ከትምህርት ቤትና ከክፍል ግለ - ግምገማ የተሰበሰበ መረጃ ስለጠንካራ ጎኖችና ወደፊት ትኩረት ሊደረግባቸው ስለሚገቡ ደካማ ጎኖች መረጃ ለማመንጨት ተተንትነዋል። | ት/ቤቱ ጥንካሬውንና መሻሻል የሚገባውን ለመለየት የሚያስችለው መረጃ ሙሉ በሙሉ በመሰብሰብ ትንተና አካሂዷል። በዚህም መሠረት መሻሻል የሚገባቸውን የቅድሚያ ትኩረት ጉዳዮች ተለይተዋል። ለሚመለከታቸውም የት/ቤቱ አባላት ኃላፊነት ሰጥቷል። | ት/ቤቱ ጥንካሬውንና መሻሻል የሚገባውን ለመለየት የሚያስችለውን መረጃ ሰብስቦ ዕቅድ ለማውጣት የሚያስችለው ትንተና አካሂዷል። | ት/ቤቱ ጥንካሬውንና ማሻሻል የሚገባውን ለመለየት ዘዴ ቀይሶ መረጃ መሰብሰብ ጀምሯል። የማሻሻያ ዕቅድ ለማውጣት የሚያስችለው ትንተና ግን ገና አላካሄደም። | ት/ቤቱ ጥንካሬውንና ማሻሻል የሚገባውን ለመለየት የሚያስችል ዘዴ ገና አልቀየሰም። | |
| 1.2.4 | ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎች የሚጠብቀው ከፍተኛ ውጤትና የባህርይ ለውጥ እንዳሉት ከዳሰሳ ጥናት የተገኙ መረጃዎች አረጋግጠዋል። | ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤትና የባህርይ ለውጥ እንዲያስመዘግቡ የተቀመጠውን ዓላማ እውን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የትምህርት ቤቱ እምነትና ባህል ሆኗል። ከዳሰሳ የተገኘው መረጃ በጣም ከፍተኛ ሆኖ ይታያል። | ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤትና የባህርይ ለውጥ እንዲያስመዘግቡ የተቀመጠውን ዓላማ እውን ለማድረግ በአመዛኙ የትምህርት ቤቱ እምነት/ባህል ሆኗል። ከዳሰሳ የተገኘው መረጃ ከፍተኛ ሆኖ ይታያል። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ስለሚጠበቀው ከፍተኛ ውጤትና ባህርይ አንዳንድ የማስተዋወቅ ሥራ በመሥራቱ ከዳሰሳ የተገኘው መረጃ መጠነኛ ሆኖ ይታያል። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ይጠብቃል። ነገር ግን ከተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንደሚጠበቅ የማስተዋወቅ ሥራ ገና አልተሠራም። ከዳሰሳ የተገኘው መረጃ ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። | |

**ስታንዳርድ 5፡- ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ለትምህርት ተነሳሽነት ያላቸውና በንቃት የሚሳተፉ ሆነዋል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/ የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.2.5 | መምህራን አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በመጠቀማቸው የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ አድጓል። | ሁሉም መምህራን አሳታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ስለሚጠቀሙ በትምህርት ክፍለ ጊዜያት የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ በጣም ከፍተኛ መሆኑን የክትትልና ግምገማ መዛግብት ያስረዳሉ። | አብዛኛው መምህራን አሳታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ስለሚጠቀሙ በትምህርት ክፍለ ጊዜያት የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን የክትትልና ግምገማ መዛግብት ያስረዳሉ። | የተወሰኑ መምህራን አሳታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ስለሚጠቀሙ በትምህርት ክፍለ ጊዜያት የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ጥሩ ጅማሪ መኖሩ የክትትልና ግምገማ መዛግብት ያስረዳሉ። | መምህራን አሳታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴ የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ ማሳደግ እንደሚችል ቢያምኑም መጠቀም አልጀመሩም። | |
| 1.2.6 | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ደከም ያሉበትን ሁኔታዎች በመለየት የማሻሻያ ስልት ቀይሶ በመንቀሳቀሱ ውጤታቸው ተሻሽሏል | ት/ቤቱ መደበኛ በሆነ ሁኔታ ተማሪዎች በትምህርታቸው ደከም ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚጠቀምበትን ስልትና ያወጣውን ዕቅድ ተግባራዊ አድርጓል። በየጊዜውም ይገመግማል። ግምገማውም ያተኮረው ከሚፈለገው ስታንዳርድ እና ከመማር ጥራት አኳያ ነው። (ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል) | ት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርታቸው ደከም ያሉበትን ሁኔታዎች ለይቶ ለማወቅ ስልት በቀየሰውና ባወጣው ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል። (ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል) | ት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርታቸው ደከም ያሉበትን ሁኔታዎች ለይቶ ለማወቅ የሚቻልበትን ዕቅድ አውጥቷል አንዳንድ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምሯል። | ት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርታቸው ደከም ያሉበትን ሁኔታዎች ለይቶ የሚሻሻልበትን ስልት መቀየስ እንዳለበት ያምናል። ሆኖም በዚህ ረገድ ምንም ዕቅድ አላወጣም። | |

**ስታንዳርድ 6፡- የግምገማ ተግባራትና ሪፖርቶች ለተሻለ የትምህርት አሰጣጥና የመማር ውጤት መምጣት ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.2.7 | መምህራን የተማሪዎቹን ዕድሜና የክፍል ደረጃ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን የተማሪዎቹን | አብዛኞቹ የትምህርት ቤቱ መምህራን | የትምህርት ቤቱ ውስን መምህራን የተማሪዎቹን | ት/ቤቱ መምህራን የተማሪዎቹን ዕድሜና | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች በመጠቀማቸው የትምህርት አሰጣጣቸውን አሻሽለዋል። | ዕድሜና የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች አቅደው በተግባር ማዋላቸውንና ይህንኑ የሚያረጋግጡ ዘላቂና አስተማማኝ የሆኑ ዘዴዎች ት/ቤቱ አሉት። | በታቀደው ዕቅድ መሠረት የተማሪዎቹን ዕድሜ የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች መጠቀም የሚችሉበትን ስልት በተግባር ላይ አውለዋል። | ዕድሜና የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች እየተጠቀሙ ሲሆን ትምህርት ቤቱ ሥልጠና ለመስጠት ዕቅድ አውጥቷል። | የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተገቢነት ያላቸው የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎች መጠቀም እንዳለባቸው ያውቃል። ሆኖም በዚህ ረገድ እስካሁን ያደረገው እንቅስቃሴ የለም። | |
| 1.2.8 | ከግምገማ የተገኙ መረጃዎችን ትምህርት ቤቱ የወደፊት እቅድና ፕሮግራም ለመንደፍ ተጠቅሞባቸዋል። | ት/ቤቱ የተማሪዎች የግምገማ ውጤቶችን የሚያደራጅበትና ትንተና የሚያካሂድበት ቀልጣፋ ስልት አለው። መረጃውንም ቅድሚያ ትኩረት በማውጣት ለት/ቤቱ ስትራተጂክ ዕቅድ እና ፕሮግራም ዝግጅት በመደበኛነት ይጠቀምበታል። አሰራሩም የትምህርት ቤቱ ባህል ሆኗል። | ት/ቤቱ የተማሪዎች የግምገማ ውጤቶችን አደራጅቶ ትንተና አካሂዷል። ቅድሚያ ትኩረት የሚሹትን ለይቶ ለስትራተጂክ ዕቅድ እና ፕሮግራም ተግባር አውሏል። | ት/ቤቱ የተማሪዎችን የግምገማ ውጤቶችን ትንተና ለማካሄድ በሚያመች መልኩ አደራጅቶ አስቀምጧል። ትንተና ለማካሄድ ዕቅድ አውጥቷል፣ ስልትም ቀይሷል። | ት/ቤቱ የግምገማ ውጤት ለወደፊት ዕቅድ እንደሚረዳ ያውቃል። ነገር ግን የተገኙትን ውጤቶች ተንትኖ ለት/ቤቱ ስትራተጂክ ዕቅድ አላዋለም። ለወደፊቱ ይህን ለማድረግ አስቧል። | |
| 1.2.9 | ለተማሪዎች ተገቢው ግብረ-መልስ (feed back) ለመስጠቱ ማረጋገጫ መንገድ አለ። | ሁሉም መምህራን ተከታታይ ግምገማ በማድረግ ለተማሪዎቻቸው ወቅቱን የጠበቀ ግብረ-መልስ የመስጠት ተግባርን እንደባህል አዳብረውታል። ይህም ከተማሪዎች በተሰበሰበ መረጃ ተረጋግጧል። | አብዛኛው መምህራን ተከታታይ ግምገማ በማድረግ ለተማሪዎቻቸው ወቅቱን የጠበቀ ግብረ-መልስ የመስጠት ተግባርን እንደባህል አዳብረውታል። ይህም ከተማሪዎች በተሰበሰበ መረጃ ተረጋግጧል። | የተወሰኑ መምህራን የውጤት ግብረ-መልስ ለተማሪዎች ይሰጣሉ። ትምህርት ቤቱም መከታተያ ስርዓት በመዘርጋት ለመተግበር እቅድ አዘጋጅቷል። | መምህራን የተማሪዎች የትምህርት ውጤት ግብረ-መልስ እንደሚያስፈልግ ቢያምኑም ታቅዶና አሰራር ሥርዓት ተዘርግቶለት አልተተገበረም። | |
| 1.2.10 | ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት (መማር) ግምገማ ላይ ተሳትፈዋል፤ የራሳቸውንም ትምህርት (መማር) በመገምገም | ሁሉም የት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት አሰጣጥና በራሳቸው ትምህርት አቀባበል ግምገማ ላይ በመሳተፍ የማሻሻያ ግብ ጥለው የመንቀሳቀስ ባህል | አብዛኛው የት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት አሰጣጥና በራሳቸው ትምህርት አቀባበል ግምገማ ላይ በመሳተፍ የማሻሻያ | የተወሰኑ የት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት አሰጣጥና በራሳቸው ትምህርት አቀባበል ግምገማ ላይ በመሳተፍ የማሻሻያ ግብ ጥለው | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን በትምህርት አሰጣጥና በራሳቸው ትምህርት አቀባበል ግምገማ ላይ በመሳተፍ የማሻሻያ ግብ ጥሎ | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ለወደፊቱ ትምህርታቸው አቅደዋል (ግብ ጥለዋል)። | ማዳበራቸው በክትትልና ግምገማ ሰነድ ተረጋግጧል። | ግብ ጥለው የመንቀሳቀስ ባህል ማዳበራቸው በክትትልና ግምገማ ሰነድ ተረጋግጧል። | የመንቀሳቀስ ባህል ማዳበራቸው በክትትልና ግምገማ ሰነድ ተረጋግጧል። | መንቀሳቀስ እንደሚገባ ቢያምንም ተግባራዊ አላደረገም። | |
| 1.2.11 | የግምገማ ውጤትና መረጃ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን መማርና ማስተማሩን ለማሻሻል ጥቅም ላይ ውሏል። | በት/ቤቱ ተከታታይ ምዘና (ግምገማ) የተገኘ ግብረ-መልስ ለተማሪዎች መማር እና ለማስተማሩ ተግባር መሻሻል መጠቀም በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ተግባር ሆኗል። መምህራን በቋሚነት የተማሪዎችን የተከታታይና የማጠቃለያ ግምገማ ውጤቶችን በመመዝገብ ለማሻሻሉ ተግባር አውለዋል። ት/ቤቱም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ያበረታታል። | መምህራን የተከታታይ ምዘና (ግምገማ) የተገኘ ግብረ-መልስ ለመማር ማስተማሩ መሻሻል ተግባር ማዋል ጀምረዋል። ት/ቤቱ በነደፈው ስልት መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ያበረታታልም። | ት/ቤቱ መምህራን የተከታታይ ምዘና (ግምገማ) የተገኘ ግብረ-መልስ ለመማርና ማስተማሩ መሻሻል ተግባር እንዲያውሉ ማበረታታት ጀምሯል። ለወደፊት ይህንን ተግባር በሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት አውጥቷል። | መምህራን የማጠቃለያ የግምገማ መረጃን ብቻ የመማር ሁኔታ ለማሻሻል ተጠቅመዋል። ት/ቤቱ ለወደፊት ተከታታይ ምዘና (ግምገማ) መጠቀም እንደሚኖርበት ያውቃል። | |
| 1.2.12 | ለወላጆች የተደረገው ሪፖርት ስለልጆቻቸው የትምህርት ውጤትና ስላሳዩት የባህሪ ለውጥ እድገት ገንቢ አስተያየቶችን የሰጠ ነው። | ሪፖርቶች ልጆቻቸው ስላሳዩት የውጤትና የባህሪ ለውጥ (መሻሻል) የተሟላ መረጃ የሰጡ ናቸው። ከወላጆች የተሰበሰበው መረጃ እርካታቸው በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | ሪፖርቶች ልጆቻቸው ስላሳዩት የውጤትና የባህሪ ለውጥ (መሻሻል) ጥሩ መረጃ የሰጡ ናቸው። ከወላጆች የተሰበሰበው መረጃ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | ሪፖቶች ልጆቻቸው ስላሳዩት የውጤትና የባህሪ ለውጥ (መሻሻል) የተወሰነ መረጃ የሰጡ ናቸው።ከወላጆች የተሰበሰበው መረጃ መጠነኛ መሆኑን ያሳያል። | ሪፖርቶች አጭርና ልጆቻቸው ስላሳዩት የውጤት ለውጥ (መሻሻል በቂ መረጃ የሰጡ አይደሉም የተሰበሰቡት መረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል) | |

**ንዑስ ጉዳይ 1.3፦ ሥርዓተ ትምህርት**

**ስታንዳርድ 7፦** ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣ አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ ለመሆኑ የመመርመርና የማሻሻል ሂደቶች አሉ።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 1.3.1 | የሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች (ሲለበስ፣ የተማሪ መፅሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያ፣ የማጣቃሻ መፃሕፍትና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች) ከተማሪዎቹ ዕድገት ደረጃና ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ፣ ከማናቸውም አድልዎ ነፃ የሆኑ ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ተገቢነት ያላቸውና የሚያሳትፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በመምህራን ግምገማና ማሻሻያ ተደርጎባቸው ጥቅም ላይ ውለዋል። | ሁሉም መምህራን በሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች ጥራትና ተገቢነት ላይ ግምገማ በማድረግ የማሻሻያ ሃሳብ የመስጠት ተግባር በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም በክትትልና ግምገማ መዛግብት ተረጋግጧል። | አብዛኛው መምህራን በሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች ጥራትና ተገቢነት ላይ ግምገማ በማድረግ የማሻሻያ ሃሳብ የመስጠት ተግባር በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም በክትትልና ግምገማ መዛግብት ተረጋግጧል። | የተወሰኑ መምህራን በሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች ጥራትና ተገቢነት ላይ ግምገማ በማድረግ የማሻሻያ ሃሳብ የመስጠት ተግባር በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም በክትትልና ግምገማ መዛግብት ተረጋግጧል። | የትምህርት ቤቱ የሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች ጥራትና ተገቢነት መገምገምና ማሻሻያ መስጠት እንዳለበት ቢያምንም የተጨበጠ ተግባር አላከናወነም። | |

## ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 2፦ ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ

ሁሉንም በዕኩልነት የሚያይ፣ መልካም አቀባበል የሚያደርግ ማህበረሰብ ያለው ትምህርት ቤት ርስ በርስ በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነቶችን ያጎለብታል። ለእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጐት ተስማሚ የሆነና ምቹ የሆነ አካባቢ ሊፈጠር ይገባል። ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የደህንነት ስሜት ከተሰማቸው ትምህርታቸውን በፍላጎት ይከታተላሉ። ተማሪዎች ስለትምህርታቸው ጉዳይ ውሳኔ በመስጠት ተሳትፈው የራሳቸውን አስተዋጽዖ ማበርከት እንዲችሉ አቅማቸው እንዲጎለብትና ድምፃቸውም ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ ይገባል።

**ንዑስ ጉዳይ 2.1፦** የትምህርት ቤት ፋሲሊት (school facilities)

**ስታንዳርድ 8፦** ት/ቤቱ ለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ የጠበቀ ፋሲሊቲዎችን በማሟላቱ የት/ቤቱ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ ለማከናወን፣ ተማሪዎችም ለመማር አስችሏቸዋል።

| ተራ ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | X |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመስራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 2.1.1 | ት/ቤቱ በአጥር የተከበረ ሳቢና ማራኪ የሆነ ግቢ ያለው በመሆኑ ተማሪዎች አዘወትረው በትምህርት ገበታቸው እንዲገኙ አስችሏል። | የት/ቤቱ ይዞታ ተረጋግጦ በአጥር የተከበረ በተለያዩ ተክሎች ተውበ የተማሪዎችን ቀልብ የሚስብ ለመሆኑ በምልከታ ተረጋግጧል። | የት/ቤቱ ይዞታ ተረጋግጦ በአጥር የተከበረና በተለያዩ ተክሎች ለማስዋብ ጥረት ላይ መሆኑ በምልከታ ተረጋግጧል። | ት/ቤቱ ይዞታን ለማስከበርና ውበቱንም ለማስጠበቅ አንዳንድ እንቅስቃሴ ላይ ጀምሯል። | ት/ቤቱ ይዞታን ማስከበርና ውበቱንም ማስጠበቅ ግንዛቤ ያለው ቢሆንም የተከናወነ ተግባር የለውም። | |
| 2.1.2 | መማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁና ምቹ አካባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት አነሳስቷል። | ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነሳሱ፣ ምቹና የክፍል ተማሪ ጥመርታ ስታንዳርድን የጠበቁ መሆናቸው በምልከታ ተረጋግጧል። | አብዛኛዎቹ የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁ ምቹና የክፍል ተማሪ ጥመርታ ስታንዳርዱን የጠበቁ መሆናቸውን በምልከታም ተረጋግጧል። | የት/ቤቱ የተወሰኑት የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁ ምቹና የክፍል ተማሪ ጥመርታ ስታንዳርድን የጠበቁ መሆናቸው ይታያል። | ት/ቤቱ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁና ምቹ የመማሪያ ክፍሎች መኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን ት/ቤቱ ቢገነዘብም እስካሁን የተሠራ ሥራ የለም። | |
| 2.1.3 | ት/ቤቱ ለመማር ማስተማር ሥራ ደጋፊ የሆኑና ደረጃቸውን የጠበቁ በተገቢው ቁሳቁሶች የተሟሉ (የትም/ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ቤተ-ሙከራ | ት/ቤቱ ለመማር ማስተማር ሥራ ደጋፊ የሆኑ፣ ደረጃቸውን የጠበቁና በተገቢው ቁሳቁሶች የተሟሉ (የትም/ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ቤተ-ሙከራ /ሳይንስ ኪት፣ ቤተ-መፃህፍት፣ የስፖርት | ት/ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ ደጋፊ የሆኑ፣ ደረጃቸውን የጠበቁና በተገቢው ቁሳቁሶች የተሟሉ (የትም/ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ቤተ-ሙከራ | ት/ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ ደጋፊ የሆኑ፣ ደረጃቸውን የጠበቁና በተገቢው ቁሳቁሶች በከፊል የተሟሉ (የትም/ ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ቤተ-ሙከራ | ት/ቤቱ ለመማር ማስተማር ሥራ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎችና ቁሳቁሶችን ማደራጀትና ማሟላት እንደሚገባው ቢያምንም ተግባራዊ ሥራ እንቅስቃሴ አልጀመረም። | |

| ተራ ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመስራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | /ሣይንስ ኪት፣ ቤተ-መፃህፍት፣ የስፖርት ሜዳዎችና የመምህራን ማረፊያ ወዘተ) ያሉት በመሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተሳካ ሆኗል። | ሜዳዎችንና የመምህራን ማረፊያ ወዘተ) አደራጅቶ በጣም ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን ከምልከታና ከክትትል መዛግብት ተረጋግጧል። | /ሳይንስ ኪት፣ ቤተ-መፃህፍት፣ ስፖርት ሜዳዎችና የመምህራን ማረፊያ ወዘተ) አደራጅቶ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን ከምልከታና ክትትል መዛግብት ተረጋግጧል። | /የሳይንስ ኪት፣ ቤተ-መፃህፍት፣ ስፖርት ሜዳዎችና የመምህራን ማረፊያ ወዘተ) አደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። | | |
| 2.1.4 | በት/ቤቱ ደረጃቸውን የጠበቁ እና በፆታ የተለዩ መፀዳጃ ቤቶች የውሃ አገልግሎት ተዘጋጅተው ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ግልጋሎት በመስጠታቸው ተጠቃሚዎች ረክተዋል፣ | ትምህርት ቤቱ ከተገልጋዮች ቁጥር እና ከፆታ አኳያ በቂ ግልጋሎት ሊሠጡ የሚችሉ የውሃ እና መፀዳጃ ቤት አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል። ይህም ከተጠቃሚዎች ከተገኘ የጥናት ውጤት እርካታቸው በጣም በከፍተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ ከተገልጋዮች ቁጥር እና ከፆታ አኳያ ግልጋሎት ሊሠጡ የሚችሉ የውሃ እና መፀዳጃ ቤት አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል። ይህም ከተጠቃሚዎች ከተገኘ የጥናት ውጤት እርካታቸው ከፍተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። | ት/ቤቱ ግልጋሎት ሊሠጡ የሚችሉ የውሃና መፀዳጃ ቤት በተወሰነ ደረጃ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል። መጠነኛ እርካታም እንደተገኘ ተገልጋዮች አረጋግጠዋል። | ት/ቤቱ የውሃና የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት መሟላት እንዳለበት የተገነዘበ ቢሆንም አገልግሎቱን ለመስጠት ያከናወነው ተግባር የለም። | |
| 2.1.5 | በት/ቤቱ ለመማር ማስተማሩ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ /ሬዲዮ፣ ፕላዝማ፣ ቴፕ ኮምፒዩተር ወዘተ/ ተሟልተው ግልጋሎት ሰጥተዋል። | ት/ቤቱ ከተማሪዎች ቁጥር ጋር የሚመጣጠኑ የICT ማቴሪያሎች /ሬዲዮ፣ ቴፕ፣ ኮምፒዩተር፣ ፕላዝማ/ አሟልቶ አገልግሎት ሰጥቷል። ይህም በተማሪዎች ዘንድ በጣም ከፍተኛ እርካታ እንዳስገኘ በዳሰሳ ጥናት ተረጋግጧል። | ት/ቤቱ ከተማሪዎች ቁጥር ጋር የሚመጣጠኑ የICT ማቴሪያሎች /ሬዲዮ፣ ቴፕ፣ ኮምፒዩተር፣ ፕላዝማ/ አሟልቶ አገልግሎት ሰጥቷል። ይህ በተማሪዎች ዘንድ ከፍተኛ እርካታ እንዳስገኘ በደሰሳ ጥናት ተረጋግጧል። | ት/ቤቱ የICT ማቴሪያሎች በከፊል ተሟልቶ አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል። | በት/ቤቱ የICT ማቴሪያሎች ተሟልተው አገልግሎት መስጠታቸው የሚታመን ቢሆንም ታቅዶ የተከናወነ ተግባር የለም። | |

**ንዑስ ጉዳይ 2.2፦ ተማሪን ማብቃት** (Student Empowerment)

**ስታንዳርድ 9፦ ትምህርት ቤቱ የተለያዩ አደረጃጀቶች አሰራር ሥርዓ በመዘርጋቱ በተማሪዎች ዘንድ ኃላፊነትን የመውሰድና ራስን በዲሲፕሊን የመምራት ልምድ ዳብሯል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 2.2.1 | ትምህርት ቤቱ በውሳኔዎች አሰጣጥ ላይ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደጉ የተማሪዎች ኃላፊነትን የመውሰድና በዲስፕሊን የመመራት ባህሪ ይዳብራል። ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤት ካውንስል፣ የሕፃናቶች ፓርላማ እና የክፍል ስብሰባዎች ይጠቀሳሉ። | ት/ቤቱ ተማሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተሳታፊ የሚያደርጋቸውን በርካታ ሥልቶች ዘርግቷል፤ ተማሪዎችም የሚሰጧቸው ሀሳቦች ተቀባይነት እንዳላቸውና ድምፃቸውም ተሰሚነት እንዳለው ተገንዝበዋል። በት/ቤት በተካሄደው ጥናታዊ ግምገማም የተማሪዎች እርካታ በጣም ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን ያረጋግጣል። | ት/ቤቱ ተማሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችላቸው የተወሰነ ሥልት ቀይሶ ተንቀሳቅሷል። ይህም የትምህርት ቤት የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጣይነት እንደሚኖረው ለማስቻል እቅድ ተዘርግቷል። በት/ቤት የተካሄደው ጥናታዊ ግምገማም ከፍተኛ የተማሪዎች እርካታ ከፍተኛ መኖሩን ያረጋግጣል። | ት/ቤቱ ተማሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተሳታፊ መሆን የሚያስችላቸውን አንዳንድ ሥልቶች ቀይሷል፣ ይህንንም ሁኔታ ይበልጥ ለማጐልበት የሚያስችለው እቅድ አለው። በት/ቤት በተካሄደው ጥናታዊ ግምገማም መጠነኛ የተማሪዎች እርካታ መኖሩን ያረጋግጣል። | ት/ቤቱ ተማሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ስትራተጂ ገና አልነደፈም። ሆኖም ስትራተጂው መነደፍ እንዳለበት ግንዛቤ አለው።በት/ቤት በተካሄደው ጥናታዊ ግምገማም ዝቅተኛየተማሪዎች እርካታ መኖሩን ያረጋግጣል። | |
| 2.2.2 | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን በአመራር ላይ እንዲሳተፉ ለሁሉም ፆታዎች እኩል ዕድል ሰጥቷል። (ምሳሌ ተማሪዎቹ የትምህርት ቤቱን ክለቦች በመምራት) | ት/ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአመራር ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠሩ ምክንያት ተማሪዎች በት/ቤቱ በተለያዩ አመራር ሰጪነት ቦታዎች ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል። ማረጋገጫ የክበቦች መዛግብት። | ት/ቤቱ የተማሪዎችን የአመራር ብቃት ለማሳደግ የሚያስችላቸው የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል። | ትም/ ቤቱ የተማሪዎችን የአመራር ሰጪነት ሚናን ማጐልበት የሚያስችል ዕቅድ አዘጋጅቷል። | ት/ቤቱ የተማሪዎች በአመራር ሰጪነት መሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን ቢገነዘብም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ግን ዕቅድ አውጥቶ አልተንቀሳቀስም | |
| 2.2.3 | የሥነ-ተዋልዶ ጤናና ከዚህም ጋር የተያያዙ የርስ በርስ ግንኙነት ሁኔታዎች በሁሉም ክፍል ደረጃዎች | ተማሪዎች በሥነ-ተዋልዶ ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ ለማጐልበት የሚያስችል ጠንካራ ፕሮግራም ት/ቤቱ ያለው ሲሆን ይህንኑ | ት/ቤቱ ተማሪዎችን የሥነ-ተዋልዶ ትምህርት ለማስተማር ፕሮግራም አለው። ይህንኑ በት/ቤቱ እቅዶች ውስጥ | ት/ቤቱ ተማሪዎችን የሥነ-ተዋልዶ ትምህርት ለማስተማር ፕሮግራም ዘርግቷል። ይህንን ፕሮግራም ተማሪዎች | ት/ቤቱ ተማሪዎችን የሥነ- ተዋልዶ ትምህርት እንዲማሩ ፕሮግራም ዘርግቷል። ይሁን እንጂ ይህንን ፕሮግራም | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | የትምህርት ቤቱ ፕሮግራሞች አካል ናቸው። | ፕሮግራም ተማሪዎች እንዲኖራቸው ከሚፈለገው አስተሳሰብና ሊቀበሉት ከሚገባው ኃላፊነት አንፃር ተገናዝቦ ተተግብሯል። | በማካተት የህይወት ክሂሎት ትምህርት ለማጐልበት እንቅስቃሴ ጀምሯል። | ሊኖራቸው ከሚችለው አስተሳሰብን ሊቀበሉት ከሚችሉት ሀላፊነትና ካላቸው አመለካከት ጋር አብሮ እንዲሄዱ ለማድረግ አቅዷል። | ተማሪዎች ሊኖራቸው ከሚችለው አስተሳሰብና አመለካከት ጋር ለማዛመድ አልሞከረም። | |
| 2.2.4 | የተማሪዎች ባህሪያት በተገቢው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በተለያዩ ሁኔታዎች ወይም አውዶች በግልፅ ታይቷል። | ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች ተፈላጊ  የባህሪይ እድገት መዳበር የማረዱ የተለያዩ ፕሮግራሞች በማመቻቸትና ተማሪዎችም ራሳቸውን በዲስፕሊን የመምራት ባህል በማሳደጋቸው የተማሪዎች ባህሪያት በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ከባለድርሻዎች በተደረገ ደሰሳ ጥናትና መዛግብት ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች ተፈላጊ የባህሪይ እድገት መዳበር የማረዱ የተለያዩ ፕሮግራሞች በማመቻቸትና ተማሪዎችም ራሳቸውን በዲስፕሊን የመምራት ባህል በማሳደጋቸው የተማሪዎች ባህሪያት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ከባለድርሻዎች በተደረገ ደሰሳ ጥናትና መዛግብት ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ባህሪያት ለማሳደግና ፕሮግራም በማመቻቸት ተማሪዎችም ራሳቸውን በዲስፕሊን ለመምራት እንዲችሉ በማቀድ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቷል። | ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ባህሪያት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ለማድረስ የተለያዩ ፕሮግራሞች ነድፎ መስራት እንዳለበት የተገነዘበ ቢሆንም የተከናወነ ተግባር የለም። የተማሪዎችም ባህሪያት ችግር ያለበት ነው። | |
| 2.2.5 | በመማሩ ሂደት ተማሪው ሃላፊነት የሚሰማው፣ በራሱ የሚተማመን፣ ነፃነት የሚሰማውና ተቀባይነት እንዳለው የዳሰሳ ጥናቶች አመልክተዋል። | ት/ቤቱ በአጠቃላይ ምቹ የመማሪያ ሁኔታ እንዲፈጠር በማመቻቸቱና መምህራን እና የትምህርት ቤቱ አመራር ተማሪዎች በተለያዩ ክበባትና የቡድን አመራር በንቃት እንዲሳተፉ በማድረጉ በራስ የመተማመንና ኃላፊነትን በብቃት የመወጣት ችሎታና ክህሎትን በውስጣቸው በማዳበር በሁሉም ነገር ነጻነት የሚሰማቸው ስለመሆናቸው ማረጋገጫ አለው በተማሪዎች የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት እርካታቸው በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | ትም/ ቤቱ ተማሪው ኃላፊነት የሚሰማው፣ በራሱ የሚተማመን፣ ነጻነት የሚሰማውና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ በነደፈው ዕቅድ መሠረት በርካታ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። በተማሪዎች የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት እርካታቸው ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | ተማሪው በመማሩ ሒደት ኃላፊነት የሚሰማው፣ በራሱ የሚተማመንና ነፃነት የሚሰማው እንዲሆን ለማድረግ ዕቅድ  አውጥቶ አንዳንድ  እንቅስቃሴ ማድረግ  ጀምሯል በተማረዎች  የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት እርካታቸው መጠነኛ መሆኑን ያሳያል። | ት/ቤቱ ተማሪው በመማሩ ሒደት ኃላፊነት የሚሰማው በራሱ የሚተማመን፣ ነፃነት የሚሰማውና  ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ግንዛቤ ያለው ቢሆንም ይህንን ለመተግበር አስፈላጊውን ዕቅድ አዘጋጅቶ እንቅስቃሴ እንዳልጀመረ የዳሰሳ ጥናቱ አመልክቷል። | |

**ንዑስ ጉዳይ 2.3፦ ለተማሪ የሚደረግ ድጋፍ** (student support)

**ስታንዳርድ 10፦ የትምህርት አካባቢዎች ለሁሉም ተማሪዎች ምቹ፣ የማያሰጉ፣ ደጋፊ እና የተማሪዎች ፍላጎቶች የሚያሟሉ በመሆናቸው ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ ሆነዋል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 2.3.1 | በትምህርት ቤት የሚከናወኑ ማናቸውም የትምህርት ሥራዎች ከሁሉም በላይ ቀዳሚ አድርገው የተንቀሳቀሱት የተማሪውን የመማር ፍላጎትና ውጤት ማሟላት ላይ መሆኑ ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም በላይ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት ቀዳሚ አድርጎ ወላጆችን/አሳዳጊዎችንና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በሙሉ አሳትፎና ተገቢው እቅድ ነድፎ በመሥራቱ በጣም ከፍተኛ ውጤት ተገኝቷል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም በላይ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት ቀዳሚ አድርጎ ሁሉንም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አሳትፎና ተገቢው እቅድ ነድፎ በመሥራቱ ከፍተኛ ውጤት ተገኝቷል። | ትምህርት ቤቱ የሚያከናውናቸው የትምህርት ሥራዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት መሠረት ያደረጉ ዕቅዶችን አዘጋጅቶ አንዳንድ ተግባራትን ማከናወን ጀምሯል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም በላይ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት ቀዳሚ አድርጎ መንቀሳቀስ እንዳለበት ግንዛቤ ቢኖረውም ይህንን ገቢራዊ ማድረግ የሚያስችል ስልት ገና አላዘጋጀም። | |
| 2.3.2 | ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚችሉበት እድሉ አላቸው፤ትምህርት ቤቱም በተለይ ለሴት ተማሪዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። | ት/ቤቱ ጥሩ የግምገማ ሥልት ስላለውና የወንድና የሴት ተማሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ትኩረት በመስጠቱ ምክንያት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በሙሉ ስኬታማ የመሆን እድል አጋጥሟቸዋል። | ት/ቤቱ የወንዶችና የሴት ተማሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች የሚረዳበትንና የሚደግፍበትን ስልት ነድፎ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረጉ አብዛኞቹ ተማሪዎች ስኬታማ ሆነዋል። | ት/ቤቱ ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን ዕድል ለማመቻቸትና ለማሟላት መምህራኑን ለማሰልጠን እቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። | ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ብዙ መሥራት እንዳለበት ት/ቤቱ ተገንዝቧል። ነገር ግን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ግምገማን መሠረት ያደረገ እቅድ አልተዘጋጀም። | |
| 2.3.3 | ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች የሚያደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ የትምህርት ብክነት እንዲቀንስ አድርጓል። | ትምህርት ቤቱ ከቁልፍ ባለድርሻዎች ጋር ተቀናጅቶ በዘረጋው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት | ትምህርት ቤቱ ከቁልፍ ባለድርሻዎች ጋር ተቀናጅቶ በዘረጋው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ | ትምህርት ቤቱ ከቁልፍ ባለድርሻዎች ጋር ተቀናጅቶ በዘረጋው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት | ተማሪዎች ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ ክፍል እንዳይደግሙና በሰዓቱ ወደ ት/ቤት እንዲመጡ ጥረት መደረግ | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | | አተገባበር የትምህርቱ ብክነት /ማቋረጥና መድገም/ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። | ሥርዓት አተገባበር የትምህርቱ ብክነት /ማቋረጥና መድገም/ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። | አተገባበር የትምህርቱ ብክነት /ማቋረጥና መድገም/ ጥሩ ደረጃ ቀንሷል። | እንዳለበት ት/ቤቱ ቢያውቅም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ግን አቅዶ አልተንቀሳቀሰም። | |
| 2.3.4 | ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን ብቃት አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ውጤታቸው ከፍ እንዲልና በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያስችል ሥልት በመዘርጋት ሥራ ላይ አውሏል። | ት/ ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ውጤት መሻሻል የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ ስልት ስላለው ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች እኩል የመሻሻል እድል አላቸው። የዚህ ማረጋገጫው የትምህርት ቤቱ ውጤት ትንተና መዝገብ ይሆናል። | ት/ ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ውጤት መሻሻል የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ባወጣው እቅድ መሠረት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። የዚህ ማረጋገጫም የትምህርት ቤቱ ውጤት ትንተና መዝገብ ነው። | ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ውጤት መሻሻል የሚያስችል ስልት ለማዘጋጀት አቅዷል።መረጃዎችንም በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። | በዚህ ጉዳይ ላይ ትምህርት ቤቱ ምንም መረጃ አልሰበሰበም ትንታኔም አላካሄደም። ይህንን ማድረግ እንዳለበት ግን ያውቃል። | |
| 2.3.5 | ትምህርት ቤቱ ምቹና የማያሰጋ መሆኑን ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ወላጆች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ። | ትም/ቤቱን ምቹና የማያሰጋ ለማድረግ የትም/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ወላጆች /አሳዳጊዎች/ በጋራ አቅደው በመንቀሳቀሳቸው ከትም/ቤቱ ማህበረሰብና ከወላጆች የተገኘው እርካታ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ። | ትም/ቤቱን ምቹና የማያሰጋ ለማድረግ ትም/ቤቱ አቅዶ በርካታ እንቅስቃሴዎች በማድረጉ የት/ቤቱ ማህበረሰብ እርካታ ከፍተኛ እንደሆነ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ። | ትም/ቤቱ ምቹና የማያሰጋ እንዲሆን ለማድረግ ትም/ቤቱ ዕቅድ አውጥቶ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች አድርጓል። የተሰበሰቡ መረጃዎች መጠነኛ እርካታ እንዳለ ያመለክታሉ። | ትም/ቤቱ ምቹና የማያሰጋ መሆን እንዳለበት ግንዛቤ ቢኖረውም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ አቅዶ አልተንቀሳቀሰም የተሰበሰቡ መረጃዎች። ዝቅተኛ እርካታ እንዳለ ያመለክታሉ። | |
| 2.3.6 | ት/ቤቱ የመደበው በጀት የተማሪዎችን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚወጣውን ወጪ ያካተተ መሆኑንና ለዚህም ተግባር መዋሉ ተረጋግጧል። | ወላጆች/አሳዳጊዎች በት/ቤት የልጆቻቸው ጤንነትና ደህንነት ባስተማማኝ ደረጃ የተጠበቀ መሆኑን በመገንዘባቸው ይህንኑ ይበልጥ ለማጐልበት | ት/ቤቱ የሚመድበው በጀት የተማሪዎችን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን በመገንዘብ በጀት መድቦ እንቅስቃሴ አድርጓል። የመጀመሪያ ህክምና | ለተማሪዎች ጤንነትና ደህንነት ማስጠበቂያ የሚውለውን ወጪ ት/ቤቱ ከአጠቃላይ የት/ቤቱ በጀት ውስጥ እንዲካተት አድርጓል። | ት/ቤቱ ለተማሪዎች ጤንነትና ደህንነት በጀት እንደሚያስፈልገው ቢያውቅም በትምህርት ቤቱ በጀት ውስጥ አካቶ | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | | ተጨማሪ የገንዘብ የቁሳቁስና የባለሙያ ድጋፍ የሚያደርጉበት ስልት ተዘርግቷል። | ዕርዳታ መስጫ ማዕከል፣ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ.ኤድስና የቀይ መስቀል ክበብ ጠንክሮ መንቀሳቀሱ ለዚህ ማረጋገጫ ነው። | | ተግባራዊ እንቅስቃሴ አላደረገም። | |
| 2.3.7 | የትምህርት ቤቱ የሥነ-ምግባር ደንቦች<br>• ለሰዎች መሰጠት ስለሚገባው አክብሮትና ለንብረቶች ስለሚደረገው ጥንቃቄ፤<br>• እንደ ሁከት፣ ማግለልና አድልዎ፣ ኃይል መጠቀም፣ ማስፈራራት፣ ተደባዳቢነትና የመሳሰሉት እኩይ ባህርያት ፍጹም ተቀባይነት እንደሌላቸው፤<br>• ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታትመንገዶችን(Procedures)<br>• የትምህርት ቤቱን ሕግና ደንብ የማክበር ግዴታንና ተቀባይነት ያለው (safe) ባህሪይ ማሳየት የሚገባ መሆኑን የሚገልጹና መግለጫዎች ያካተቱ ናቸው። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚተዳደሩበትና የሚመሩበት ደንብና የሥነ-ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረጉ የትም/ቤቱ ማህብረሰብ በሙሉ የተቀበላቸው የመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች በትም/ቤቱ ተረጋግጠዋል። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚተዳደሩበትና የሚመሩበት ደንብና የሥነ-ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚተዳደሩበትና የሚመሩበት ደንብና የሥነ-ምግባር መመሪያ ለማዘጋጀት አቅዷል። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚተዳደሩበትና የሚመሩበት ደንብና የሥነ -ምግባር መመሪያ ሊኖረው እንደሚገባ የተገነዘበ ቢሆንም እስከአሁን ግን ደንብና መመሪያ የለውም። | |

**ስታንዳርድ 11፡-** የልዩ ፍላጐት ተማሪዎች ዕኩል የመማር ዕድል አላቸው፤ ለውጤት እንዲበቁም በየችሎታቸው መጠን በተደረገላቸው እገዛ መሠረት ስኬታማ ሆነዋል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 2.3.8 | በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ በCPD ፕሮግራም የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተካቷል። | በመምህራን የተከታታይ ሥልጠና ፕሮግራም (CPD) እና ሌሎች ሥልጠናዎች ላይ የልዩ | በርካታ መምህራን የልዩ ትምህርት ፍላጐትን በCPD ዕቅድ ውስጥ አካተዋል፣ ባንዳንድ የልዩ ፍላጐት | ጥቂት መምህራን የልዩ ፍላጐት ትምህርትን በCPD እቅዳቸው ውስጥ አካተዋል። ትምህርት | ትምህርት ቤቱ በልዩ ፍላጐት ትምህርት የመምህራኑን እውቀት ለማጐልበትና በልዩ | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | | ፍላጐት ትምህርት መደበኛ የትኩረት አቅጣጫ ስለመሆኑ ማረጋገጫ አለ። | ትምህርት ላይ ሥልጠናዎች እየተካሄዱ ናቸው። መሻሻል የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችንም ለመለየት በማስተማሩ ሥራ ላይ ግምገማ ይካሄዳል። | ቤቱም መምህራኑ በልዩ ፍላጐት ትምህርት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ብዙ መሥራት እንዳለበት ተረድቷል። | ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅበት ያውቃል። | |
| 2.3.9 | ትምህርት ቤቱ የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራምን ለመምራት እንዲቻል የሰለጠኑ መምህራን፣ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችና ፋሲሊቲዎችን ለማሟላት ጥረት በማድረግ ፕሮግራሙን ተግባራዊ አድርጓል። | የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርትና ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ትምህረት ቤቱ ማድረግ ያለበትን ሁሉ አድርጓል። የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንን መድቧል፤ በትምህርት አሰጣጡ ላይ ክትትል ያደርጋል። ማረጋገጪው ከልዩ ፍላጐት ትምህርት መከታተያ መዝገብ ላይ ይገኛል። | ትምህርት ቤቱ ለልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያደርገው ድጋፍ፣ ቁሳቁስና ፋሲሊቲዎች አጥጋቢ ናቸው። የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ ላይ የሚደረገውን ክትትል ተከትሎና ይሄን የልዩ ፍላጐት ትምህርት ማጠናከር የሚያስችል ዕቅድ አቅዶ ተግባራዊ እያደረገ ነው። | ት/ቤቱ ለልዩ ፍላጐት ትምህርት መተግበር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንና ፋሲሊቲዎችና የሠለጠኑ የሰው ኃይል ለመሟላት እቅድ ነድፏዋል። | ት/ቤቱ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን አሟልቶ መንቀሳቀስ እንዳለበት ቢገነዘብም ዕቅድ አውጥቶ እንቅስቃሴ የጀመረበት ሁኔታ ግን የለም። | |
| 2.3.10 | የተማሪዎች ልዩ ፍላጐት ተመዝግቦ ተይዟል። ፕሮግራሞችን የማስተማር ዘዴዎችን እና ማቴሪያሎችን እንደየፍላጐታቸው ተስማሚ እንዲሆኑ በማድረግ በችሎታቸው መጠን ተምረው ውጤታማ ሆነዋል። | በህብረት የማቀድ ዘዴዎችን በመጠቀምና መረጃዎችን በመለዋወጥ ጭምር ፕሮግራሞችን የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ማቴሪያሎችን አሻሽሎ በመጠቀም /በማዘጋጀት/ ሁሉም ተማሪዎች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ተደርጓል። | ትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የማስተማር ዘዴ ለማስፈን ሥልጠናና መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል። እንዲሁም በአብዛኛው ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ በማስተማሩ ሥራ ላይ ቁጥጥር አድርጓል። | የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ማቴሪያሎችን ለማሻሻል አንዳንድ ሙከራዎች ቢኖርም ይህ ግን ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚተገበር አይደለም። ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቱ ይህንን ገቢራዊ ለማድረግ እቅድ አለው። | ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን በችሎታቸው መጠን ተምረው ውጤታማ እንዲሆኑ ፕሮግራሞች፣ የማስተማር ዘዴዎችና ማቴሪያሎች እንደየፍሎግታቸው ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል። ነገር ግን ተግባራዊ ማድረግ አልጀመረም። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 2.3.11 | ተማሪዎች ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች ስላገኙት የርካታ ደረጃ በወላጆች ላይ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች ያመለክታሉ። | በወላጆች ላይ የተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተገኘው እርካታ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | በወላጆች ላይ የተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተገኘው እርካታ አጥጋቢ ደረጃ እንደሆነ ያሳያል። | በወላጆች ላይ የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት መጠነኛ እርካታ እንደተገኘ ያሳያል። | በዳሰሳ ጥናቱ መሠረት እርካታቸው ዝቅተኛ መሆኑ ታይቷል። | |
| 2.3.12 | የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ያለ ችግር ሊጠቀሙባቸው እንዲችሉ በቀላልና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የተደራጁ ናቸው። | ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ያለችግር እንዲጠቀሙባቸው ወላጆች/ አሳዳጊዎችና ህብረተሰቡ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲሳተፉ አድርጓል። | ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ያለ ችግር እንዲጠቀሙባቸው በሚደረገው እንቅስቃሴ ወላጆች/ አሳዳጊዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርጓል። ወላጆች/አሳዳጊዎች በዚህ ዙሪያ የተሠሩት ሥራዎች ከፍተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ። | ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ያለችግር እንዲጠቀሙባቸው እገዛ አድርጐላቸዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ ሰፊውን ህብረተሰብ ለማሳተፍ ገና የታሰበበት አይደለም። ወላጆች/አሳዳጊዎች በዚህ ዙሪያ የተሠሩት ሥራዎች መጠነኛ እንደሆነ ይገልፃሉ። | ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍሎች ልዩ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ያለችግር ሊጠቀሙባቸው እንዲችሉ በቀላልና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለማደራጀት ያምናል። ነገር ግን የተከናወነ ተግባር የለም ወላጆች/አሳዳጊዎች በዚህ ዙሪያ የተሠራው ሥራ ዝቅተኛ መሆኑን ይገልፃሉ። | |

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 3፦ የትምህርት ቤት አመራር

የትምህርት ቤት አመራር ለትምህርት ቤቱ ግልጽ ራዕይ መቅረጽ እና ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር መመሪያዎችን በማውጣት ወደ ራዕዩ መምራት ይኖርበታል። ራዕዩ ተማሪን ማዕከል ያደረገና ለመምህራን ትኩረት ሰጥቶ ተከታታይ መሻሻልን የሚፈልግ ነው። አመራርና አስተዳደር የጋራ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

### ንዑስ ጉዳይ 3.1፦ ስትራተጂያዊ ራዕይ

**ስታንዳርድ 12፦** ትምህርት ቤቱ የጋራ የሆነ ራዕይ አለው። የተነደፉት ግቦችና ዓላማዎች በትምህርት ቤቱ የቅድሚያ ትኩረት ጉዳዮች ላይ ተንፀባርቀው የሚጠበቀው ውጤት አስገኝተዋል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.1.1 | የትምህርት ቤቱ ስትራተጂካዊና ዓመታዊ እቅዶች በግለ-ግምገማ ውጤት ላይ ተመስርተው በአሳታፊነት የተዘጋጁ ናቸው። | ትምህርት ቤቱ ግልጽ ራዕይ ያለው ነው። ሁሉም እቅዶች የታቀዱት ግለ-ግምገማን መሠረት በማድረግ ነው። ግለ-ግምገማውም በተገቢ መረጃ የተደገፈ ነው። | ትምህርት ቤቱ ግለ-ግምገማ አካሂዷል። የማሻሻያ ሥራ ለማቀድም በአመዛኙ ከግምገማ የተገኘውን ውጤት ተጠቅሞበታል። | ትምህርት ቤቱ ግለ ግምገማ አካሂዷል። የማሻሻያ ሥራ ለማቀድ የተወሰኑ የግምገማ ውጤቶችን ተጠቅሟል። | ትምህርት ቤቱ ዕቅድ ለማዘጋጀት ግለ-ግምገማ ማድረግ እንደሚገባም ቢያምንም ተግባራዊ እንቅስቃሴ አልጀመረም። | |
| 3.1.2 | ከትምህርት ቤቱ ራዕይና ግቦች ጋር ጎን ለጎን የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማ (professional appraisal) እና ሙያዊ ትምህርቶች አሉ። | ት/ቤቱ የነደፈውን ራዕይና ግብ ለማሳካት አብረው የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማና ሙያዊ ትምህርቶች በሚፈለገው መልኩ ገቢራዊ አድርጓል። | ትም/ቤቱ የነደፈውን ራዕይና ግብ ለማሳካት አብረው የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማና ሙያዊ ትምህርቶች መኖር እንዳለባቸው ግንዛቤ በመወሰዱ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እቅድ አቅዶና ስልት ቀይሶ በመስራት ላይ ይገኛል። | ትም/ቤቱ የነደፈውን ራዕይና ግብ ለማሳካት አብረው የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማና ሙያዊ ትምህርቶች መኖር እንዳለባቸው ግንዛቤ በመወሰዱ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እቅድ አቅዷል። | ትም/ቤቱ የነደፈውን ራዕይና ግብ ለማሳካት አብረው የሚሄዱ ሙያዊ ግምገማና ሙያዊ ትምህርቶች መኖር እንዳለባቸው ግንዛቤ ቢኖረውም ይህንን ግን አቅዶ ተግባራዊ ማድረግ አልጀመረም። | |
| 3.1.3 | በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑት | ትም/ቤቱ በስትራቴጂክ እቅድ የሚመራና የተጠናከረ | ትም/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የሚመራና | ትም/ቤቱ እቅድ አውጥቶ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች | በትም/ቤቱ የሚከናወኑ ተግባራት በቋሚነት | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ተግባራት በቋሚነትና ሳይዋዥቁ (consistently) የሚተገበሩ መሆናቸው ተረጋግጧል። | የትግበራ፣ የክትትል፣ የሪፖርትና ግብረ-መልስ ሥርዓት ስላለው ሁሉም ተግባራት ሳይዋዥቁ መተግበራቸውን ከትም/ቤቱ ሰነዶችና ከባለድርሻ አካላት የተገኘ መረጃ ያረጋግጣል። | የተጠናከረ የትግበራ፣ የክትትል፣ የሪፖርትና ግብረ-መልስ ሥርዓት ስላለው አብዛኛው ተግባራት ሳይዋዥቁ መተግበራቸውን ከትም/ቤቱ ሰነዶችና ከባለድርሻ አካላት የተገኘ መረጃ ያረጋግጣል። | ማድረግ ጀምሯል። በመሆኑም በትም/ቤቱ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ በቋሚነት ሳይዋዥቁ የሚተገበሩት መጠነኛ ስለመሆናቸው የትም/ቤቱ ማህበረሰብ አረጋግጠዋል። | ሳይዋዥቁ መተግበር የሚቻለው እስትራቴጂክ እቅድ ሲኖር መሆኑን ትም/ቤቱ ግንዛቤ ቢኖረውም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ግን የተደረገ ጥረት የለም። | |
| 3.1.4 | እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች (ethics)፣ መሪ የሆኑ መርሆዎች እና የትምህርት ቤቱ ዓላማዎች በትምህርት ቤቱ ማህባረሰብ በሞላ የታወቁ ናቸው። | መምህራንና አመራሩ በትምህርት ቤቱ እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪዎች፣ መሪ የሆኑ መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ ያዳበሩ በመሆኑ ተቀናጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት በጣም ከፍተኛ አተገባበር ያለ መሆኑ ተረጋግጧል። | መምህራንና አመራሩ በትምህርት ቤቱ እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪዎች፣ መሪ የሆኑ መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ ያዳበሩ በመሆኑ ተቀናጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት ከፍተኛ አተገባበር ያለ መሆኑ ተረጋግጧል። | መምህራንና አመራሩ በትምህርት ቤቱ እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪዎች፣ መሪ የሆኑ መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ ያዳበሩ በመሆኑ ተቀናጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት መጠነኛ አተገባበር ያለ መሆኑ ተረጋግጧል። | የትምህርት ቤቱ እሴቶች፣ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች፣ መሪ የሆኑ መርሆዎችና ዓላማዎችን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ እንዳለበት የተገነዘበ ቢሆንም ከዳሰሳዊ ጥናቱ ዝቅተኛ አፈፃፀም መሆኑ ተረጋግጧል። | |
| 3.1.5 | የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ እቅድ ለማሳወቅና ለመተግበር የሚያስችሉ ስልቶች በግልፅ ተቀምጠዋል። | የትም/ቤቱን አጠቃላይ እስትራቴጂካዊ እቅድ ለትም/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ለማሳወቅና ለመተግበር የሚያስችል ስልት ተዘርግቶ እስትራቴጂክ እቅዱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ በተመደበለት ገንዘብና የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል። | የትም/ቤቱን አጠቃላይ እስትራቴጂካዊ እቅድ ለትም/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ለማሳወቅና ለመተግበር የሚያስችል ስልት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመካሄድ ላይ ነው። | የትም/ቤቱን አጠቃላይ እስትራቴጂካዊ እቅድ ለትም/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ለማሳወቅና ለመተግበር የሚያስችል ስልት ተቀይሶ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። | የትም/ቤቱን አጠቃላይ እቅድ ለትም/ቤቱ ማህበረሰብና ለወላጆች /አሳዳጊዎች/ ለማሳወቅ የሚያስችል ስልት በግልጽ መቀመጥ እንዳለበት ትም/ቤቱ ግንዛቤ ቢኖረውም ይህንን ግን ተግባራዊ አላደረገም። | |
| 3.1.6 | የትምህርት ቤቱ አመራር ሰጭ አካላት በግልጽ | አመራሩ ራዕይ ያለው የሚሠራውን የሚያውቅና ከፍተኛ ጉጉት ያለው ነው። የማሻሻያ | ትምህርት ቤቱ በግልጽ የተቀመጡ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች | ትምህርት ቤቱ በግልጽ የተቀመጡ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች | ትምህርተ ቤቱ ስታንዳርድንና ትምህርት ቤት ለማሻሻል ትኩረት | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ስለተቀመጡት ግቦችና ስለሚጠበቁ ከፍተኛ ውጤቶች አዘውትረው ይገልፃሉ፤ የተገኙ መሻሻሎችንም ተከታትለዋል። | ግቦችም ግልጽና ከፍተኛ ስታንዳርድ ላይ ያተኩሩ ከመሆናቸውም በላይ ስለሚጠበቁት ከፍተኛ ውጤቶች ለትቤቱ ማበረሰብ መግለፅ የዘወትር ተግባር ነው። እቅዶችም በየጊዜው ክትትል ይደረግባቸዋል። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት ክንውኑ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል። | አሉት። አመራር ሰጪዎችም ለበርካታ ጊዜያት ለትቤቱ ማህበረሰብ ይህንኑ ገልፀዋል። የተገኙ መሻሻሎችንም በተነደፈው ስልት መሠረት በመከታተል ላይ ናቸው። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት ክንውኑ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል። | ቢኖሩትም ለትቤቱ ማህበረሰብ የሚገልፁት አልፎ አልፎ ነው። የተገኙ መሻሻሎችን ስልት ነድፈው ለመከታተል እንቅስቃሴ ጀምረዋል። በመምህራንና በተማሪዎች ላይ የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት ክንውኑ መጠነኛ እንደሆነ ያሳያል። | ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያምናል። ይሁን እንጂ ስታንዳርድን ከፍ ለማድረግና የተገኘውን መሻሻል ለመከታተል ገና አልተንቀሳቀሰም። | |

## ንዑስ ጉዳይ 3.2፦ የመሪነት ባህርይ

## ስታንዳርድ 13፦ ቀጣይነት ያለውና በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ቤት መሻሻል መኖሩ ተረጋግጧል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.2.1 | ት/ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የነደፋቸውን የት/ቤት መሻሻል ቅድሚያ ትኩረቶች ውጤታማነት ለመተንተንና ለማወቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። | ት/ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የነደፋቸውን የት/ቤት መሻሻል የቅድሚያ ትኩረቶች ውጤታማነት ለመተንተንና ለማወቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ለማዋላቸው የተደረገ የዳሰሳ ጥናትና የመረጃ ሰነድ ያስረዳል። | ት/ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የነደፋቸውን የት/ቤት መሻሻል የቅድሚያ ትኩረቶች ውጤታማነት ለመተንተንና ለማወቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአብዛኛው ጥቅም ላይ ለማዋላቸው የተደረገ የዳሰሳ ጥናትና የመረጃ ሰነድ ያስረዳል። | ት/ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የነደፋቸውን የት/ቤት መሻሻል የቅድሚያ ትኩረቶች ውጤታማነት ለመተንተንና ለማወቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በከፊል ጥቅም ላይ ለማዋላቸው የተደረገ የዳሰሳ ጥናትና የመረጃ ሰነድ ያስረዳል። | ት/ቤቱ ማህበረሰቡን በማማከር የት/ቤት መሻሻል ቅድሚያ ትኩረቶችን መንደፍ ውጤታማነታቸውን ለማወቅ መረጃዎችን በሙሉ መጠቀም እንደሚገባው የተገነዘበ ቢሆንም ያከናወነው ተግባር የለም። | |
| 3.2.2 | በተከታታይ የተመዘገቡ መረጃዎች (Longitudinal Data) የተማሪዎች ውጤቶች | የተማሪዎች ውጤት ከመነሻው ነጥብ ጋር ሲነፃፀር አሁን የደረሱበት | የተማሪዎች ውጤት ከመነሻው ነጥብ ጋር ሲነፃፀር አሁን የደረሱበት | የተማሪዎች ውጤት ከመነሻው ነጥብ ጋር ሲነፃፀር አሁን | የተማሪዎች ውጤቶች ከመጀመሪያው ነጥብ ጋር ሲነፃፀር ምን ያህል | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | መሻሻላቸውን ያንፀባርቃሉ። ይህም የውጭ አካል (External validation) በተደረገው ግምገማ ተረጋግጧል። | በጣም ከፍተኛ መሻሻሎች ስለመኖራቸው ትምህርት ቤቱ ማረጋገጫዎች አሉት። | ከፍተኛ መሻሻሎች እንዳሉ ትምህርት ቤቱ ማረጋገጫ አለው። የተሰበሰቡ መረጃዎችም ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። | የደረሱበት መጠነ ኛ መሻሻሎች እንዳሉ ትምህርት ቤቱ ማረጋገጫ አለው። | እንደተሻሻሉ ለማወቅ ለንጽጽር የሚረዳውን የመጀመሪያውን የመነሻ ነጥብ ለመዳሰስ የሚያስችል መረጃ ገና አልተሰበሰበም። | |

**ስታንዳርድ 14፦** ትምህርት ቤቱ የእርስ በርስ የሙያ መማማሪያ የሚካሄድበት ተቋም በመሆኑ የመምህራንና አመራሩ ሙያዊ ብቃት ተሻሽሏል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.2.3 | የት/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን አካቷል። | የት/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን ሙሉ በሙሉ አካቷል። | የት/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን አብዛኛው አካቷል። | የት/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን በተወሰነ መልኩ አካቷል። | የት/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የቅድሚያ ትኩረቶችን ሙሉ በሙሉ አላካተተም። | |
| 3.2.4 | ለትምህርት ቤቱ መምህራን የተሻለ ልምድ ባላቸው መምህራን ሥልጠና/እገዛ (coaching and mentoring) የሚደረግላቸው ሥርዓት በመዘርጋቱ የመምህራን | የትምህርት ቤቱ የሙያዊ የዕቅድ አካል የሆነ የተደራጀ የምልከታ፣ የማማከር፣ የማመቻቸትና የሥልጠና ሥርዓት ተዘርግቶ ለአዲስና ለነባር መምህራን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል። | የትምህርት ቤቱ የሙያዊ የዕቅድ አካል የሆነ የተደራጀ የምልከታ፣ የማማከር፣ የማመቻቸትና የሥልጠና ሥርዓት ተዘርግቶ ለአዲስና ለነባር መምህራን በአብዛኛው ተግባራዊ ሆኗል። | የትምህርት ቤቱ የሙያዊ የዕቅድ አካል የሆነ የተደራጀ የምልከታ፣ የማማከር፣ የማመቻቸትና የሥልጠና ሥርዓት ተዘርግቶ ለአዲስና ለነባር መምህራን በመጠኑ ተግባራዊ ሆኗል። | በትምህርት ቤት የተሻለ ልምድ ባላቸው መምህራን ሥልጠናና እገዛ የመስጠት ሂደት ገና አልተጀመረም። ነገር ግን ይህን የማድረግ ሂደት የመምህራንን ልምድ ለማሻሻል | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ሙያዊ ብቃት ተሻሽሏል። | | | | አስተዋጽኦ እንዳለው ትምህርት ቤቱ ተገንዝቧል። | |
| 3.2.5 | የትም/ቤቱ አመራር የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይተዋል፤ እንዲሁም የአመራር አባላቱ በሥልጠና ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ችለዋል። | የትም/ቤት አመራር ኃላፊዎች በሙሉ የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይተዋል። በሥልጠና ፕሮግራም የወደፊት ሙያቸውን እንዲያበለጽጉ የተሻለ ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል። **መረጃው** የሥልጠና ሪከርድ ነው። | በታቀደው መሠረት የአብዛኛዎቹ የትም/ቤት አመራር ኃላፊዎች የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይ ተዋል። በዚሁ መሠረት በሥልጠና ፕሮግራሞች ተሳትፈዋል። መረጃው የሥልጠና ሪከርድ ነው። | ይህ እንቅስቃሴ በአሁኑ ጊዜ በግለሰብ ስምምነት ላይ የተመሠረተ እንጂ ግልጽ የሆነ ሥርዓት የለም። ለወደፊቱ ለመተግበር በትምህርት ቤቱ በኩል እየታቀደ ነው። | ይህ በትምህርት ቤቱ በኩል ገና አልታሰበም። | |

**ስታንዳርድ 15፦** የት/ቤቱ ማኅበረሰብ የርስ በርስ ግንኙነቶች በመተማመንና በሥራ ባልደረባነት (Collegiality) ላይ የተመሠረተ መሆኑ ጤናማ የሥራ አካባቢ ፈጥሯል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.2.6 | በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል አዎንታዊ፣ ገንቢ፣ ግልጽነት የተሞላበትና በእኩልነት የተመሰረተ ግንኙነቶች መስፈናቸውን በመምህራንና | በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ያለው አዎንታዊ ግንኙነት በጣም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ መሆኑን በመምህራን፣ በወላጆችና በተማሪዎች ላይ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ተረጋግጧል። | በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ያሉት አዎንታዊ ግንኙነቶች ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ መሆኑን በመምህራን፣ በወላጆችና በተማሪዎች ላይ የተካሄዱ የዳሳሰ ጥናቶች አረጋግጠዋል። | በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ያሉት አዎንታዊ ግንኙነቶች መጠነኛ መሆኑን በተመለከተ በመምህራን፣ በወላጆችና በተማሪዎች ላይ የተካሄዱ የዳሳሰ | በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ያሉት ግንኙነቶች ዝቅተኛ መሆኑ በተመለከተ በመምህራን፣ በወላጆችና በተማሪዎች ላይ የተካሄዱ የዳሳሰ ጥናቶች አረጋግጠዋል። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | በተማሪዎች በሠራተኞችና በወላጆች ላይ የተካሄዱ የዳሳሰ ጥናቶች አረጋግጠዋል። | | | ጥናቶች አረጋግጠዋል። | | |
| 3.2.7 | ትምህርት ቤቱ የአሠራርና የግጭት አፈታት ሂደቶችን የሚገልጽ ሙያዊ ደንብ/ህግ አለው። | ትም/ቤቱ የሙያዊ አሠራርና የግጭት አፈታት ደንብ (ሕግ) በመከተል በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች በወቅቱ የመፍታት ሥራዎችን በሙሉ በተግባር አሳይቷል። ይህም በየጊዜው የተወሰዱትን እርምጃዎች ከት/ቤቱ ቃለ ጉባኤና ሪፖርቶች ተረጋግጧል። | ትም/ቤቱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ሙያዊ አሠራርና የግጭት አፈታት ሕግና ደንብ ያለው ሲሆን በአብዛኛው እየተተገበረ ነው። | ትም/ቤቱ ሙያዊ የአሠራርና የግጭት አፈታት ደንብና ሕግ አለው፣ አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታትም አልፎ አልፎ ደንቡን በሥራ ላይ ያውለዋል። | ትም/ቤቱ ሙያዊ የአሠራርና የግጭት አፈታት ሕግና ደንብ ቢኖረውም በሥራ ላይ አላዋለም። | |

**ስታንዳርድ 16፡- ሁሉም ባለድርሻዎች ለተማሪዎች የትምህርት ውጤት ተጠያቂ መሆናቸውን በመቀበል ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.2.8 | ፕሮግራሞችና የተገኙ | የትምህርት ቤቱ | የትምህርት ቤቱ መምህራንና | ትምህርት ቤቱ የተገኙ | ትምህርት ቤቱ ይህንን | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ስታንዳርዶች ዘላቂነት ያላቸው፣ አስተማማኝ የሆኑ፣ መረጋገጥ የሚችሉ እና ተጨባጭ ውጤቶችን የሚያንፀባርቁ ለመሆናቸው የትምህርት ቤቱ አመራርና መምህራን የማረጋገጥ ሙያዊ ኃላፊነት አለባቸው። | መምህራንና ሠራተኞች ባለው የሙያ ሥነ ምግባር መሠረት ሙያቸውን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ትምህርት ቤቱ ይጠብቃል። የተገኙ ስታንደርዶች ነፃ አስተማማኝና መረጋገጥ የሚቻል ትክክለኛ ውጤቶችን እንደሚያሳዩ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት በቦታው አለ። ይህንን ለማረጋገጥ እንዲያስችል በተማሪዎችና በወላጆች ላይ የተካሄደ ደሰሳዊ ጥናት በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። | ሠራተኞች ሙያውን ተከትለው ሥራቸውን እንደሚያከናውኑ ትምህርት ቤቱ ያምናል። ነገር ግን ይህን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት በትምህርት ቤት እንደሌለ ያውቃል። የተገኙ ስታንዳርዶች ትክክለኛ ውጤቶችን ስለማንጸባረቃቸው ማጤን እንዳለበትና ስትራቴጂዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸውና፣ የሥነ ምግባር መመሪያ መቀረጽ እንዳለበት ትምህርት ቤቱ ተገንዝቦ በመሥራት ላይ ነው። በተማሪዎችና በወላጆች የተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት አተገባበሩ ይህንን በከፍተኛ ደረጃ አስቀምጧል። | ስታንዳርዶች ትክክለኛ ውጤቶችን የሚንፀባርቁ ስለመሆናቸው፣ መምህራንና ሠራተኞች ሙያውን ተከትለው እንደሚሠሩ እርግጠኛ ሆኖ መረጃ ለማቅረብ ይቸገራል። ይህን በውጤት ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ እንደሆነና የሙያዊ ሥነ-ምግባር መኖር አንዳለበት ትምህርት ቤቱ ይገነዘባል። የተማሪዎችና የወላጆች ዳሰሳዊ ጥናት አተገባበሩ ይህንን መጠነኛ ደረጃ አስቀምጧል። | ለማረጋገጥ የተዘጋጀ ሥልት የሌለው ቢሆንም ይህ መጠናከር እንዳለበትና የሙያዊ ሥነ-ምግባር መኖር እንዳለበት ትምህርት ቤቱ ያምናል። የተማሪዎችና የወላጆች ዳሰሳዊ ጥናት ይህንን በዝቅተኛ ደረጃ አስቀምጧል። | |
| 3.2.9 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የልዩ ፍላጐት ትምህርት ስትራቴጂ በመተግበር፣ በማስተባበር፣ በመቆጣጠርና በመገምገም ሙያዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል። | የልዩ ፍላጐት ትምህርት ስትራቴጂ ተከታትሎ ሥራ ላይ እንዲውል የሚያደርግና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የትምህርት ቤት መምህር ተመድቧል። መረጃ የልዩ ፍላጐት ትምህርት እንዲከታተል ከተመደቡ መምህራን የተገኘ ቃለ መጠይቅ ነው። | ትምህርት ቤቱ አልፍ አልፎ ቁጥጥር የሚያካሂድና ይህንኑ ኃላፊነት የሚወጣ መምህር ለመመደብ በአለው ፍላጎት መሰረት ለአንዳንድ የትምህርት ቤቱ መምህራን ሥልጠና ሰጥቷል። | አልፎ አልፎ የሚካሄድ የቁጥጥር ሥርዓት አለው ሆኖም የልዩ ፍላጐት ትምህርት ዕቅድ ለማውጣትና ይህንኑ የሚከታተል መምህር ለመመደብ ትምህርት ቤቱ አቅዷል። | የልዩ ፍላጐት ትምህርትን ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ በትምህርት ቤቱ የለም። ነገር ግን መኖር እንዳለበት ትምህርት ቤቱ ያውቃል። | |
| 3.2.10 | በውጭ አካል የትክክለኛነት ማረጋገጫ (External validation) | የውጭ አካል የትክክለኛነት ማረጋገጫ እንዳመለከተው የትምህርት ቤቱ ግለ | በውጭ አካል የተደረገው የትክክለኛነት ማረጋገጫ ግምገማ ሪፖርት እንዳመለከተው የት/ቤቱ ግለ | የተደረገው የትክክለኛነት ማረጋገጫ መረጃ እንደሚያሳየው የት/ቤቱ | በውጪ አካል የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሪፖርት እንደሚጠቁመው የትምህርት ቤቱ ግለ- | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | የትምህርት ቤቱ ግለ ግምገማ፣ የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶችና ፕሮሲጀሮች ትክክለኛነት ጥራት ተረጋግጧል። | ግምገማ፣ የዕቅድ ሂደቶችና ፕሮሲጀሮች በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘታቸው ተረጋግጧል። ማረጋገጫው የግምገማ መረጃ ሪፖርት (ዶክመንት) ነው። | ግምገማ፣ የዕቅድ ሂደቶችና የአፈፃፀም ሥልቶች ከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ያሳያል። ማረጋገጫው የግምገማ መረጃ ሪፖርት (ዶክመንት) ነው። | ግለ-ግምገማና የዕቅድ የአፈፃፀም ሂደቶች መጠነኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ይጠቁማል። ማረጋገጫው የግምገማ መረጃ ሪፖርት (ዶክመንት) ነው። | ግምገማና የዕቅድ ዝግጅነት ክንውን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታል። ማረጋገጫው የግምገማ መረጃ ሪፖርት (ዶክመንት) ነው። | |
| 3.2.11 | መምህራን የተማሪዎችን የእድገት (የመሻሻል) ደረጃ ከሚጠበቁ ውጤቶች(Expected outcomes) ጋር በማነፃፀር የሚያዩበት ቋሚ የሆኑ መንገዶች አሏቸው። | በትምህርት ቤቱ ግምገማ ሂደት መሠረት ተማሪዎች ያሳዩት መሻሻል ከሚጠበቀው ውጤት አኳያ በማነፃፀር መምህራን የሚያዩበት ቋሚ የሆነ መንገድ አላቸው። ይህም ከትምህርት ቤቱ ክትትልና ግምገማ መዝገቦች ተረጋግጠዋል። | ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን መሻሻል በማነፃፀር መገመገም የሚያስችለው ስትራቴጂ ቀይሶ መተግበር ጀምሯል። ለዚህም የግምገማ ሰነዶች መረጃ ናቸው። | ትምህርት ቤቱ የግምገማ አሰራር ሥርዓት ባይኖረውም የመማር ማስተማር ሂደትን ለማሻሻል ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አምኖ መንቀሳቀስ ጀምሯል። | ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን እድገት (መሻሻል) ውጤቶችን ከሚጠበቀው ደረጃ ጋር ለማነጻጸር የሚያስችል መረጃ መሰብሰቢያ መዘርጋት እንዳለበት ቢገነዘብም ተግባራዊ አላደረገውም። | |

**ስታንዳርድ 17፦** የትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትና አስተዳደራዊ ተግባራት የጋራ ክንውን በመሆናቸው በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል የሥራ አንድነት ሰፍኗል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.2.12 | የወላጅ-መምህር ህብረት (P.T.A)፣ የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች የት/ቤት መሻሻል ኮሚቴና የተማሪዎች ተወካዮች ካውንስል አካላት በትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥና ሂደት ላይ በመሳተፋቸው የሥራ አንድነት ተፈጥሯል። | በትምህርት ቤት ውሳኔ አሰጣጥንና አመራር ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች በሚፈለገው ደረጃ ተሳትፈዋል። ለዚህም ማረጋገጫው የመምህራንና ሠራተኞች የተማሪዎች፣ የወላጆች የህብረተሰቡ ዳሰሳዊ ጥናትና የስብሰባ ቃለጉባኤ በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን አሳይቷል። | በትምህርት ቤት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ አብዛኛዎቹ ባለድርሻዎችና ወ.መ.ህ በጥሩ ሁኔታ ተሳትፈዋል። ለዚህም ማረጋገጫው የመምህራንና ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና የወላጆች የህብረተሰብ ዳሰሳዊ ጥናትና የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን አሳይቷል። | የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች በውሳኔ አሰጣጥና በሥራ አመራር በተወሰነ ደረጃ የሚሳተፉ ሲሆን ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ባለድርሻዎች ለማሳተፍ አቅዷል። የመምህራንና ሠራተኞች፣ የተማሪዎችና የህብረተሰብ ዳሰሳ ጥናት በመጠነኛ ደረጃ አስቀምጧል። | ባለድርሻዎችንና የወላጅ መምህር ህብረት በትምህርት ቤት ውሳኔ አሰጣጥ የመሳተፍ ሥርዓት አልተጀመረም። | |
| 3.2.13 | የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች በግልጽ የተብራሩ፣ በማስረጃ የተደገፈ በቀጣይነት የሚተገበሩ ናቸው፤ የሂደቱ ውጤቶችም ተመዝግበዋል። | ት/ቤቱ የሚሰጣቸውን የውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች በግልጽ የተብራሩ፣ በማስረጃ የተደገፉና በቀጣይነት የሚተገበሩ እንዲሆኑ አድርጐአቸዋል፤ የሂደቱ ውጤቶችም በሚገባ ተመዝግበዋል። | ት/ቤቱ የሚያስተላለፍውን የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት በተብራራና በማስረጃ ተደግፎ በቀጣይነት የሚተገበሩ እንዲሆን ለማድረግ በነደፈው ሥልት መሠረት በአብዛኛው ተግባራዊ እያደረገ ነው። | የት/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት በማስረጃ የተደገፈና የተብራራ እንዲሆንና በቀጣይነትም ለመተግበርና ውጤቱን ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሥልቶችን ነድፎ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ጀምሮአል። | የት/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች በማስረጃ የተደገፉ፣ በግልጽ የተብራሩ እና በቀጣይነትም የሚተገበሩ መሆን እንደሚገባቸው ግንዛቤ ቢኖርም የተጀመረ እንቅስቃሴ ግን የለም። | |

**ንዑስ ጉዳይ 3.3፦ የትምህርት ቤት አመራር/አስተዳደር**

**ስታንዳርድ 18፦** የሪሶርስ አስተዳደር/አመራር የትምህርት ፕሮግራሞችንና የትምህርቱን እድገት የሚደግፍ በመሆኑ የአሠራር ውጤታማነት ጐልብቷል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.3.1 | ትምህርት ቤቱ ከክለስተር ማዕከል እና ከሌሎች የአካባቢው ተቋሞች ሪሶርሶችንና በተለይም የሠለጠኑ ባለሙያዎችን በመጠቀሙ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሻሽሏል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የሪሶርሶችና የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የመማር ማስተማር ሂደት ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳላቸው በመገንዘብ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ሥራ ላይ አውሏቸዋል። **መረጃ** የትምህርት ቤት መዝገብ ፣ቃለ መጠይቅ ከአካባቢ ድርጅቶች ጋር | ትም/ቤቱ በአካባቢ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የሪሶርሶችና የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የመማር ማስተማሩን እንቅስቃሴ ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳላቸው በመገንዘብ ዕቅድ አውጥቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢ ደረጃ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ሊጠቀም እንደሚችል በመገንዘብ ይህንኑ የትምህርት ቤት የትኩረት ዕቅድ አካል ለማድረግ አንዳንድ ተግባራትን ጀምሯል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የሪሶርሶችና የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ለመጠቀም እንደሚችል ያውቃል። በዚህ መሠረት ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ከለየ በኋላ ለማቀድ ተዘጋጅቷል። | |
| 3.3.2 | የሰው፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ሪሶርሶች ቅድሚያ ትኩረት ሊሚሰጣቸውና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ በሚደግፍ መልኩ ሁኔታ ተመርቷል፣ ጥቅም ላይም ይውላሉ። | የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ሪሶርሶች ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸውና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ በሚያስችል መልኩ በመመራት በጣም በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ በመዋላቸው የተማሪዎች ውጤት ተሻሽሏል። | የሰው፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ሪሶርሶች ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸውና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ በሚያስችል መልኩ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ በመዋላቸው የተማሪዎች ውጤት ተሻሽሏል። | የሰው፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ሪሶርሶቹ ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸውና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ በሚደግፍ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል በሚያስችል ሁኔታ ላይ ዕቅድ ተነድፏል። | በዚህ ላይ ተገቢው ግንዛቤ ያለ ቢሆንም ዕቅድ ወጥቶ ተግባራዊ አልተደረገም። | |

**ስታንዳርድ 19፦ በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ውስጠ ደንብ፣ መመሪያዎችና አሰራር ሥርዓቶች ተደራጅተው ሥራ ላይ በመዋላቸው የተጠናከረ አሰራር ሰፍኗል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.3.3 | የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መመሪያዎችን፣ ባህርይንና ዲሲፕሊንን፣ ከፆታና ከዘር ዳራ አኳያ እኩል የሆነ የምቹ ዕድሎች አጠቃቀምን ያካተቱ ናቸው። | የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ ከትምህርት ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች ጋር በትብብር የተዘጋጀ ነው። የትምህርት ቤት አመራርና በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ ማንኛቸውም ተግባራትን አካቶ ተዘጋጅቷል። **መረጃ** የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ | የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ ማዘጋጀት ለትምህርቱ ሥራ መሻሻል ቅድሚያ መሆኑን በመገንዘብ ይህንኑ ውስጠ ደንብ ቀርፆ ተግባራዊ እያደረገ ነው። **መረጃ** የትምህርት ቤቱ ውስጠ ደንብ | ትምህርት ቤቱ ውስጠ ደንብ ገና አላዘጋጀም ሆኖም ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ ለማዘጋጀት እቅድ አውጥቷል። | ውስጠ ደንብ መቅረጽ ለመማር ማስተማር ሒደት መሻሻል አስተዋጽኦ እንዳለው ትምህርት ቤቱ ግንዛቤ አለው በዚሁ መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት ውስጠ ደንብ ለማዘጋጀት ሃሳብ አለው። | |
| 3.3.4 | የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ በሰነድነት ተመዝግቦ ተይዟል (documented)፤ እንዲሁም ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተሻሽሎ በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ ውሏል። | ከክልሎችና ከአገር ፖሊሲ ቅድሚያ የሚሰጠውን ጉዳይ በመለየት ከሥርዓተ ትምህርት፣ ከትምህርትና ሥልጠና አንጻር በመገመገም ትምህርት ቤቱ የራሱን ውስጠ ደንብ በመገመገም ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር አሻሽሎ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቅሞበታል። **መረጃ** የመሻሻል ውስጠ ደንብ | የተዘጋጀውን የትምህርት ቤቱን ውስጠ ደንብ ለማሻሻል በየጊዜው በመገምገም የመሻሻል ሂደትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። **መረጃ** የመሻሻል ውስጠ ደንብ | ትምህርት ቤቱ ውስጠ ደንብ አዘጋጅቷል። ነገር ግን ሀገር አቀፍና ክልላዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ ጀምሯል። **መረጃ** የመሻሻል ውስጠ ደንብ | ውስጠ ደንብ መቅረጽ ለመማር ማስተማር ሒደት አስተዋጽኦ እንዳለው ትምህርት ቤቱ ግንዛቤ አለው በዚሁ መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት ውስጠ ደንብ ለማሻሻል አልጀመረም። **መረጃ** የመሻሻል ውስጠ ደንብ | |
| 3.3.5 | የትምህርት ቤት ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች፣ ከትምህርት | የት/ቤቱ ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች ከትምህርት ቤቱ መርሆዎችና እሴቶች ጋር | የት/ቤቱ ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች ከትምህርት ቤቱ | የት/ቤቱ ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች ከትምህርት ቤቱ | የት/ቤት ውስጠ ደንብ ከአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች፣ ከትምህርት ቤቱ | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | ቤቱ መርሀዎችና እሴቶች ጋር በመጣጣሙ የተጠናከረ አሰራር ሰፍኗል። | የመጣጣሙ ደረጃው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ውጤታማ አሰራር ተፈጥሯል። | መርሀዎችና እሴቶች ጋር የመጣጣሙ ደረጃው ከፍተኛ በመሆኑ ውጤታማ አሰራር ተፈጥሯል። | መርሀዎችና እሴቶች ጋር የመጣጣሙ ደረጃው መጠነኛ ነው። | መርሀዎችና እሴቶች ጋር የመጣጣሙ ደረጃ ዝቅተኛ ነው። | |

**ስታንዳርድ 20፡-** በትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር ውጤታማ የሆነ ግንኙነት (communication) መኖሩ ተረጋግጧል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 3.3.6 | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር መደበኛና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት (Communication) በመፈጠሩ የተገልጋይ እርካታን አስገኝቷል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር መደበኛና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት በመፈጠሩ የተገልጋዮች እርካታ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር መደበኛና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት በመፈጠሩ የተገልጋዮች እርካታ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። | ትምህርት ቤቱ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር መደበኛና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት በመፈጠሩ የተገልጋዮች እርካታ በመጠነኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። | ትምህርት ቤቱ የዳበረ ግንኙነት እንደሌለው ይታወቃል። የወላጆች የማህበረሰብ ዳሰሳ (ጥናት) ይህን ዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ አሳይቷል። | |

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 4፦ የህብረተሰብ ተሳትፎ

ጥራት ያለው አጋርነትንና (Partnership) የግንኙነት መረብን ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር መፍጠር ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ከህብረተሰቡ ጋር ለማቀራረብ (ለማገናኘት) ያስችላቸዋል። እውነተኛና ቀጣይነት ያለው አጋርነት ትምህርት ቤቶች ለህብረተሰቡ መረጃዎች ለመስጠትና ህብረተሰቡ ለሚጠብቃቸው ትልሞች (Expectations) ምላሽ ለመስጠት ይረዳቸዋል።

**ንዑስ ጉዳይ 4.1፦ ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር አብሮ መሥራት** (Partnership with parents and careers)

**ስታንዳርድ 21፦ ወላጆችና አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳዮች በንቃት መሳተፋቸው የተማሪዎች መማር አጐልብቷል።**

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 4.1.1 | የወላጆች ተሳትፎ ለመደገፍ የተዘረጉ ተቋማዊ መዋቅሮች አሉ። ት/ቤቱ በሚጠራው ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉም ተበረታትተዋል። | የወላጆች ተሳትፎ ለመደገፍ የተዘረጉ አስተማማኝ መሠረት ያላቸው ተቋማዊ መዋቅሮች አሉ። ወላጆች/ አሳዳጊዎች ስለትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ሙሉ በሙሉ እንደሚገለጽላቸው እነርሱም በዝግጅቱ ላይ እንደሚገኙ አረጋግጠዋል። ለዚህም መረጃ በወላጅ ላይ የተካሄደ ዳሰሳዊ ጥናት በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧል። | የወላጆች ተሳትፎ ለመደገፍ የተዘረጉ አስተማማኝ መሠረት ያላቸው ተቋማዊ መዋቅሮች አሉ። ወላጆች/ አሳዳጊዎች ስለትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም እንደሚገለጽላቸው እነርሱም በዝግጅቱ ላይ እንደሚገኙ አረጋግጠዋል። ለዚህም መረጃ በወላጅ ላይ የተካሄደ ዳሰሳዊ ጥናት ከፍተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧል። | የወላጆች ተሳትፎ ለመደገፍ የተዘረጉ አስተማማኝ መሠረት ያላቸው ተቋማዊ መዋቅሮች አሉ። ወላጆች/ አሳዳጊዎች ስለትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም እንደሚገለጽላቸው እነርሱም በዝግጅቱ ላይ እንደሚገኙ አረጋግጠዋል። ለዚህም መረጃ በወላጅ ላይ የተካሄደ ዳሰሳዊ ጥናት መጠነኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧል። | የወላጆች ተሳትፎ ለመደገፍ የተዘረጉ ተቋማዊ መዋቅሮች የሉም። ወላጆች በትምህርት ቤቱ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ መረጃ ለማግኘት ይፈልጋሉ። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ መረጃ አያገኙም። እንዲሁም አልፎ አልፎ በትምህርት ቤቱ ዘንድ ተቀባይነት አያገኙም መረጃ የወላጆች ዳሰሳ ጥናት ይህን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣል። | |
| 4.1.2 | ወላጆች የልጆቻቸውን የቤት ሥራ በመመልከት አስተያየት ሰጥተዋል። | ሁሉም ወላጆች በልጆቻቸው የቤት ሥራ ላይ አስተያየት እንዲሰጡና ከመምህራን ጋር ውይይት እንዲኖራቸው የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ አፈፃፀሙ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል። **መረጃ** የተማሪዎች የቤት ሥራ መሥሪያ ደብተር | ትም/ቤቱ ወላጆች በልጆቻቸው የቤት ሥራ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ አፈፃፀሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። **መረጃ** የተማሪዎች የቤት ሥራ መሥሪያ ደብተር | ትም/ቤቱ ወላጆች በልጆቻቸው የቤት ሥራ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ አፈፃፀሙ መጠነኛ ነው። **መረጃ** የተማሪዎች የቤት ሥራ መሥሪያ ደብተር | ትምህርት ቤቱ ወላጆች በልጆቻቸው የቤት ሥራ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳለባቸው ያምናል። ነገር ግን የማበረታታት ሥርዓት አልዘረጋም። | |

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| | | | | | | |
| 4.1.3 | በትምህርት ቤቱ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች የመረጃዎች ልውውጥ የወላጆች ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። | በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና የመረጃ ልውውጦች በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የወላጆች /አሳዳጊዎች/ ተሳትፎ እንዳለ የት/ቤቱ መረጃ ያሳያል። | በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና የመረጃ ልውውጦች በርካታ ቁጥር ያላቸው የወላጆች /አሳዳጊዎች/ ተሳትፎ እንዳለ የት/ቤቱ መረጃ ያሳያል። | በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና የመረጃ ልውውጦች መጠነኛ ቁጥር ያላቸው የወላጆች /አሳዳጊዎች/ ተሳትፎ እንዳለ የት/ቤቱ መረጃ ያሳያል። | በትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና የመረጃ ልውውጦች የወላጆች /አሳዳጊዎች/ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። | |

## ስታንዳርድ 22፦ በትምህርት ቤቱና በወላጆች/አሳዳጊዎች መካከል የተፈጠረ ውጤታማ ግንኙነት የተማሪዎች መማርን የሚያበረታታና የሚያግዝ ሆኗል።

| ተ.ቁ. | የትግበራ ጠቋሚዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | x |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ | በመሥራት ላይ ያለ | በመጀመር ላይ ያለ | በዝግጅት ላይ ያለ | ተጨባጭነት የሌለው/የሚታይ ተግባር የሌለው |
| 4.1.4 | የተማሪን ፕሮግራሞችና ውጤቶች ሪፖርት ማድረጊያ መደበኛ የሆነ የጊዜ መርሐ-ግብር አለ። | በትምህርት ቤቱና በወላጆች መካከል የዳበረና ተከታታይ የሆነ የሪፖርት ግንኙነት አለ።<br><br>**መረጃ** በወላጆች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት የሪፖርቱ ግንኙነቱ ሂደት ይህን በጣም ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ ተረጋግጧል። | በትምህርት ቤቱና በወላጆች መካከል ያለው የሪፖርት ግንኙነት በታቀደው መሠረት በተሻሻለና ሥርዓት ባለው መንገድ ተግባራዊ ሆኗል።<br><br>**መረጃ** በወላጆች ዳሰሳ ጥናት ይህን ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ ተረጋግጧል። | በትምህርት ቤትና በወላጆች መካከል አልፎ አልፎ ግንኙነት አለ። ሆኖም በመደበኛነት የተሻሻለና የዳበረ ሥርዓት መኖር እንዳለበት ትምህርት ቤቱ በማመን ዕቅድ አውጥቷል።<br><br>**መረጃ** የወላጆች ዳሰሳ ጥናት ደረጃውን መጠነኛ እንደሆነ ያሳያል። | በትምህርት ቤትና በወላጆች መካከል የተማሪን ውጤቶች ሪፖርት ግንኙነት የለም። ይህም መሆን እንደሌለበት ትምህርት ቤቱ ይገነዘባል።<br><br>**መረጃ** የወላጆች ዳሰሳዊ ጥናት ይህንን በዝቅተኛ ደረጃ አስቀምጧል። | |
